*Ethiop.j.lang.cult.commun. 2025, 10*(1): 312-345
*Open Access Licensed under Creative Commons:*
*CC BY-NC-ND 4.0*

*Faculty of Humanities-Bahir Dar University*
*ISSN: 2518-2919*
DOI 10.20372/ejlcc.v10i1.2183

**Original Research** **Open Access**

# Content analysis of oral poems performance on agricultural inputs of farmers in Borena district

**Seid Yimam***
*PhD candidate, Addis Ababa University, Ethiopia*

**Zerihun Asfaw**

*Associate Professor, Addis Ababa University, Ethiopia*

**Mohammed Ali**

*Assistant Professor, Addis Ababa University, Ethiopia*

**Corresponding Author: yimamseid59@gmail.com*

## Abstract

The main objective of this study is to conduct a content analysis on the oral poem performed by farmers in Borena district when using chemical fertilizer, compost, herbicide, and terracing in their farm land to increase their productivity. The study followed a qualitative research method, and 15 farmers were selected through purposive and snow ball sampling techniques and the necessary data for the study were collected from the field through interviews. In addition, field observations and document reviews served as data collection method. The data collected through these methods were captured through note books, audio recordings, photographs, video cameras and then organized by type and analyzed using functional and performance theories, as well as descriptive methods. The results of the data analysis indicated that farmers engaged in agricultural activities praised the fertilizer in oral poems for being able to be productive by using chemical fertilizer that are suitable and beneficial for their crops, which are manufactured in factories and are a mixture of various ingredients. The compost which is prepared with indigenous knowledge has been praised in oral poetry for increasing productivity. The herbicide which increases the farmers' productivity has been praised in the poem. The farmers praised the work of the terraces for its great benefits in protecting the fertility of the soil from various natural and man – made hazards and increasing productivity. Finally, the researcher suggested that other folklore researchers should widely collect, document and analyze the oral poems spoken by the farmers in the district where the study was conducted, on the resources that can increase productivity.

*Ethiop.j.lang.cult.commun. 2025, 10*(1): 312-345
*Open Access Licensed under Creative Commons:*
*CC BY-NC-ND 4.0*
*Faculty of Humanities-Bahir Dar University*
*ISSN: 2518-2919*
DOI 10.20372/ejlcc.v10i1.2183

# በግብርና ግብዓቶች ላይ የተከወኑ ቃል ግጥሞች ይዘት ትንተና በቦረና ወረዳ አርሶ አደሮች ማሳያነት

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በቦረና ወረዳ የሚገኙ አርሶ አደሮች ምርታማነታቸውን ለማሳደግ የኬሚካል ማዳበሪያ፣ ብስባሽ (Compost)፣ ፀረ ዐረምና የዕርከን ሥራ የተባሉትን ግብዓቶች በማሳዎቻቸው ላይ ሲያከናውኑ የሚገጥሟቸውን ቃል ግጥሞች መተንተን ነው። ጥናቱ ዓይነታዊ የምርምር ዘዴን የተከተለ ሲሆን፣ በዓላማ ተኮር እና በጠቋሚ የንሞና ዘዴዎች ከተመረጡ 15 ሰዎች ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች በቃለ መጠይቅ ከመስክ ተሰብስበዋል። ከዚህ በተጨማሪ የመስክ ምልከታና ሰነድ ፍተሻ በመረጃ መሰብሰቢያነት አገልግለዋል። በእነዚህ ዘዴዎች የተሰበሰቡት መረጃዎች በማስታወሻ ደብተር፣ በመቅረጸ ድምፅ፣ በፎቶና በቪዲዮ ካሜራዎች ከተያዙ በኋላ በዓይነት በዓይነት ተደራጅተው በተግባራዊና በክዋኔያዊ ንድፈ ሐሳቦች፣ እንዲሁም በገላጭ ስልት ተተንትነዋል። ከመረጃ ትንተናው የተገኙት ውጤቶች እንዳመላከቱት በግብርና ሥራ ላይ የተሰማሩት አርሶ አደሮች በማሳቸው ላይ ለሰብላቸው ተስማሚና ጠቀሜታ ያለውን፣ በፋብሪካ ተመርቶ የሚቀርበውን እና የልዩ ልዩ ንጥረ ነገሮች ውሑድ የኾነውን የኬሚካል ማዳበሪያ ተጠቅመው ምርታማ ለመኾን በመቻላቸው ማዳበሪያውን በቃል ግጥም አወድሰውታል። ሀገር በቀል በኾነው ዕውቀት የሚዘጋጀው ብስባሽም ምርታማነትን በማሳደጉ የተነሣ በቃል ግጥም ተሞግሷል። ለአርሶ አደሮቹ ባለ ውለታ የኾነው ፀረ ዐረም ኬሚካልም በቃል ግጥም ተወድሷል። የዕርከን ሥራም ቢኾን የዐፈርን ለምነት ከተለያዩ ተፈጥሯዊና ሰው ሠራሽ አደጋዎች ተከላክሎ ምርታማነትን በማሳደግ ረገድ ያለው ፋይዳ ከፍተኛ በመኾኑ አርሶ አደሮቹ በቃል ግጥም አመስግነውታል። በመጨረሻም ሌሎች የፎክሎር ተመራማሪዎች ጥናቱ በተካሄደበት ወረዳ የሚገኙ አርሶ አደሮች ምርታቸውን ሊያሳድጉ በሚችሉ ግብዓቶች ላይ የተናገሯቸውን ቃል ግጥሞች በስፋት ሰብስበው ትንተና ቢያካሂዱባቸው የሚል የይሁንታ ሐሳብ በአጥኚው ቀርቧል።

**Key words:** productivity, chemical fertilizer, compost, herbicide, terracing

**Citations:** Yimam, S., Asfaw, Z. & Ali, M. (2025). Content analysis of oral poems performance on agricultural inputs of farmers in Borena district. *Ethiopian Journal of language, Culture and Communication.10* (1).312-345.
DOI 10.20372/ejlcc.v10i1.2183

*Submitted: January 2024* | *Revised: May 2025* | *Accepted:June 2025*

**©2025 Author(s). All rights reserve**

# መግቢያ

ቃል ግጥም በአንድም ኾነ በሌላ መንገድ የማኅበራዊ፣ የፖለቲካዊና የኢኮኖሚያዊ እውነታዎች መግለጫ ጥበብ ነው (Kamla-Raj, 2007)፡፡ በዓለም ላይ በተለያዩ ከዋኞች የሚቀርቡት ቃል ግጥሞች ለፈጣሪ ምስጋናን ለማቅረብ፣ በማኅበረሰቡ ውስጥ ከሚታዩት ፍርሃቶች፣ ከግጭቶች፣ ወዘተ. ራስን ለመጠበቅ ያገለግላሉ (Alembi, 2002)፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ታሪክን የመመዝገብ ወይም ሰንዶ የማስቀመጥና ፖለቲካዊ ሚናን የመጫወት ፋይዳ አላቸው (Finnegan, 1970)፡፡ Kabira እና Mutahi (1988) በበኩላቸው ቃል ግጥሞች ተማሪዎችን የማስተማር፣ መረጃዎችን የማቀበል፣ የማዝናናት፣ ባህልን የማሳደግና ለሚቀጥለው ትውልድ የማስተላለፍ፣ የመምከርና የማሰልጠን አገልግሎት እንዳላቸው ገልጸዋል፡፡

የቃል ግጥምም ሆነ አጠቃላይ የሥነ ቃል ዘርፎች ጥናት በምሥራቅ አፍሪካ የተጀመረው በ0ሥራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ አካባቢ መኾኑን Peek እና Yankah (2004)፣ እንደዚሁም Finnegan (2012) ገልጸዋል፡፡ በዚያን ወቅት ሃይማኖታቸውን ለማስፋፋትና የቅኝ ግዛት ዓላማቸውን ከግብ ለማድረስ ፍላጎት የነበራቸው አውሮፓውያን ተጓዦች፣ የወንጌል ሰባኪዎች፣ የቋንቋና የሥነ ሰብ ምሁራን ቃል ግጥሞችን፣ ተረካዎችን፣ ምሳሌያዊ አነጋገሮችን እና ሌሎች ዘውጎችን ሰብስበዋል (Finnegan, 1974)፡፡ ከአውሮፓውያኑ በተጨማሪ አፍሪካውያኑም ራሳቸው የሥነ ቃል ዘርፎችን በማጥናት መጻሕፍት ያሳተሙ መኾኑን በዘርፉ ላይ ጥናት ያካኼዱት Peek and Yankah (2004) ገልጸዋል፡፡

ከእነዚህ በተጨማሪ ከዛሬ ኀምሳ ዓመታት ወዲህ በFinnegan (1970) “Oral Literature in Africa” እና (1977) “Oral Poetry: Its Nature, Significance and social Context”፣ እንደዚሁም በOkpewho (1992) “African Oral Literature” የሚሉ በቃል ግጥሞች ላይ ፈር ቀዳጅ የኾኑ ምርምሮች ተሠርተው እያሉ በአፍሪካ ጠቃሚ የኾነ የቃል ግጥም ጥናት አለ ወይ? (Does Africa have Poetry worth Studying?) በማለት በአውሮፓውያኑ የተነሡ ሙግቶች አሉ (Alembi, 2002)፡፡ ለምሁራኑ ሙግት መነሻ የኾነው ዋናው ምክንያት ቃል ግጥም ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰና የተሻሻለ ባህል ወይም ሥልጣኔ መግለጫ በመኾኑ ነው፡፡ አውሮፓውያኑ ግን የአፍሪካ ሕዝቦች ልማዳዊ (traditional) በመኾናቸው፣ እስካሁን ድረስ በችግሮች የተተበተቡና በጨለማ ውስጥ የሚኖሩ ፍጡራን አድርገው በመቁጠራቸው የተነሣ ቋንቋዎቻቸውም ቢኾኑ ውስብስብ የኾነውን የቃል ግጥም አገላለጽ ቴክኒኮችን አርኪ በኾነ መንገድ ለመግለጽ ብቁ ኾነው አላደጉም (Okpewho,1985)፡፡

በአፍሪካ በመስክ ላይ የሥነ ቃል ጥናት ያደረጉ ምሁራን ግን በአህጉሯ በጣም የዳበረና በማኅበረሰቡ ውስጥም የተትረፈረፈ ቃል ግጥም መኖሩን በምርምሮቻቸው አማካይነት ስላረጋገጡ ከላይ የቀረበውን አመለካከት አልተቀበሉትም በማለት Alembi (2002) ገልጸዋል፡፡ በዚህ መሠረት በርከት ያለ ቁጥር ያላቸው አፍሪካውያን በየራሳቸው ቋንቋዎች የሥነ ቃል ጥናት ማካኼዳቸው ወጥ የኾኑ የምርምር ሥራዎች እንዲታዩ አድርጓል ማለት ይቻላል፡፡

ከ1950ዎቹ ጀምሮ በርካታ ኢትዮጵያውያንም በራሳቸው ፍላጎት ተነሣሥተው የባህል ቅርስን ለወጣቱ ትውልድ ለማስተላለፍ ባላቸው ዓላማ ቃል ግጥምንም ኾነ ልዩ ልዩ የሥነ ቃል ዘርፎችን ሰብስበው አሳትመዋል (ፈቃደ፣ 1991)፡፡ እስከ 1990ዎቹ መጨረሻ ድረስም ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል ከ137 በላይ በቃል ግጥሞች ላይ ብቻ ጥናቶች እንደተሠሩ ፈቃደ አረጋግጠዋል፡፡ እነዚህ ምሁራን ለየደረጃዎቹ የሚያበቃቸውን ዲግሪ ለማግኘት ብቻ ሳይኾን ጥናቶቻቸው ባካለሏቸው አካባቢዎች ያሉትን ቃል ግጥሞች ሰብስበው ለመተንተን ባላቸው ዓላማ ነው፡፡

በዚህ ጥናት ግን በደቡብ ወሎ ቦረና ወረዳ የሚገኙ አርሶ አደሮች ምርታማነታቸውን ለማሳደግ የኬሚካል ማዳበሪያን በዘርና በዐረም ወቅት ሲጠቀሙ፣ ብስባሽን (compost) ከዘር በፊት በማሳዎቻቸው ላይ ሲበትኑ፣ ፀረ ዐረም ኬሚካልን በበቀለው ቡቃያ ላይ ሲረጩና የማሳ ላይ እርከንን ሲሠሩ በሚያዜሟቸው ቃል ግጥሞች ላይ የይዘት ትንተና ተካሂዷል፡፡ ምክንያቱም አርሶ አደሮቹ እነዚህን ግብዓቶች በመጠቀም የምግብ ፍጆታቸውን ማሟላት፣ ገቢያቸውን ማሳደግ፣ ወዘተ. በመቻላቸው የተሰማቸውን እርካታ በቃል ግጥሞቻቸው አማካይነት ስለሚያንጸባርቁ ነው፡፡

## የጥናቱ አነሣሽ ምክንያት

በአሁኑ ወቅት ቃል ግጥምን በተመለከተ በኢትዮጵያ ውስጥ ባሉ ዩኒቨርሲቲዎች በባችለር፣ በማስተርስና በፒኤች. ዲ. ዲግሪ በርካታ የመመረቂያ ጽሑፎች ሊሠሩ እንደሚችሉ መገመት አያዳግትም፡፡ ከስፋትና ከብዛት አንጻር እነዚህን ሥራዎች በሙሉ በዚህ ጥናት ውስጥ መቃኘት የማይቻል መኾኑን አጥኚው አምኖበታል፡፡ ሆኖም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በሂዩማኒቲስ፣ በቋንቋዎች ጥናት፣ በጆርናሊዝምና በኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ በአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ እንደዚሁም በውጭ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ማኅበረሰቦች ላይ ብቻ የጥናታቸውን ወሰን አድርገው የተሠሩ ዐሥር የማስተርስና ሦስት የፒ.ኤች.ዲ. ዲግሪ፣ በድምሩ ዐሥራ

ሦስት የቃል ግጥም ጥናቶች ተቃኝተዋል፡፡ ቅኝት የተካሄደባቸው ጥናቶችም በሰርግ ሥርዓት፣ በልጃገረድ ዘፈኖች፣ በዛር ዘፈኖች፣ በለቅሶና በቀብር ሥርዓት፣ በመኸር ወቅት፣ በወፍጮ ዐውድ፣ በሊሪክ (በስሜት ነኪ)፣ በፉከራ፣ በረኀብ፣ ወዘተ. ጊዜ በተቀነቀኑ ቃል ግጥሞች ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡ እዚህ ላይ መጠቆም የምፈልገው ግብርናን በተመለከተ ለፒ.ኤች.ዲ. ዲግሪ ማሟያ የሚሆኑ ጥናቶች በክልሉ ውስጥ የተሠሩ ቢሆንም ቃል ግጥሞችን መሠረት ያደረጉ ባለመሆናቸው ቅኝት አልተካሄደባቸውም፡፡

በማሳቸው ላይ በሚጠቀሙበት ወቅት የሚያዜሟቸው ቃል ግጥሞች ከመስክ ተሰብስበው በዘውግ ከተከፋፈሉ በኋላ የይዘት ትንተና የተካሄደባቸው ጥናቶች አለመኖራቸውን በቅኝቱ ወቅት ለማረጋገጥ ችያለሁ፡፡ በዚህ ምክንያት ይህንን ጥናት ለማካኼድ ተነሣስቻለሁ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ማኅበረሰብና ባህል የተሳሰሩ እስከኾኑ ድረስ ወደፊት በማኅበረሰቡ ውስጥ ማኅበረ ኢኮኖሚያዊ እድገት ከመጣ በባህል ላይ ለውጥ መከሰቱ አይቀሬ ነው፡፡ ስለሆነም በጊዜ ሒደት በማኅበረሰቡ ውስጥ በሚኖር የኢኮኖሚ እድገት ምክንያት በወረዳው ውስጥ በአርሶ አደሮቹ የሚቀነቀኑት ቃል ግጥሞች ከመለወጣቸውና ከመረሳታቸው በፊት ተሰብስበው መጠናት አለባቸው የሚለው እምነት በውስጤ ማደሩ ሌላው የጥናቱ አነሣሽ ምክንያት ሆኗል፡፡

## የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዐቢይ ዓላማ ሰው ሠራሽ ማዳበሪያን፣ ብስባሽን፣ ፀረ ዐረምን እና ዕርከን ሥራን በተመለከተ በወሎ ቦረና ወረዳ አርሶ አደሮች የተገጠሙ ቃል ግጥሞችን በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅና በሰነድ ፍተሻ ከመስክ ሰብስቦ በፈርጅ በፈርጅ በመመደብ የይዘት ትንተና ማካሄድ ነው፡፡ ዝርዝር ዓላማዎቹ ደግሞ ቃል ግጥሞቹ በየሚከወኑባቸው አጋጣሚዎች መለየት፣ በዘውግ መከፋፈልና በይዘት መተንተን የሚሉት ናቸው፡፡

# የተዛማጅ ድርሳናት ክለሳ

በዚህ ርእሰ ጉዳይ ሥር በቃል ግጥም፣ በሥራ ቃል ግጥም ምንነትና ባሕርያት ላይ ትኩረት የተደረገ ሲኾን፣ እነዚህን ጽንሰ ሐሳቦች በሚያስተነትን መልኩ የተካኼደው ተግባርም በሚከተለው ኹኔታ በአጭሩ ቀርቧል፡፡

### ቃል ግጥም

ቃል ግጥም የአንድን ኅብረተሰብ ማኅበረ-ባህላዊ እሴቶችን ከትውልድ ወደ ትውልድ ለማስተላለፍ፣ የማኅበረሰቡን የእርስ በርስ ትስስርና የጋራ ቅርሶችን ለማጠናከር የሚያገለግል ጥበብ ነው (Anthony & Olajide, 2012)፡፡ Finnegan (1977) እንደገለጹት ቃል ግጥም ማኅበራዊ ደንቦችን፣ ታሪካዊ ክስተቶችን፣ የጋራ እሴቶችን እና ልምዶችን በማንፀባረቅ ረገድ ወሳኝ ሚና ይጫወታል፡፡ በአፍሪካ የሚኖሩ ህዝቦች በዕለት ተዕለት ኑሯቸው የሚያጋጥሟቸውን ሠናይም ሆኑ እኩይ ተግባራትን የሚያንጸባርቁት በቃል ግጥሞቻቸው ነው (Finnegan, 1970)፡፡ ኢትዮጵያም በአህጉሩ ማሕቀፍ ውስጥ የምትገኝ በመሆኗ ህዝቦቿ ሀብታቸው በሆነው ቃል ግጥም አጠቃላይ የህይወት ገጽታቸውን ሲገልጹ ይስተዋላል፡፡

Okpewho (1992) በአፍሪካ የሚገኙ የቃል ግጥም ዓይነቶችን ለይቶ ለመመደብ ችግሮች መኖራቸውን ከገለጹ በኋላ በማንኛውም ማኅበረሰብ ውስጥ የሚከወኑትን የተለያዩ የዘፈን እና የዝማሬ ዓይነቶችን ለመከፋፈል ልዩ ልዩ መስፈርቶችን መጠቀም እንደሚቻል አስረድተዋል፡፡ በዚህ መሠረት የቃል ግጥሞቹ በሚያነሡት ርእሰ ጉዳይ፣ ከዋኞቹ በሚጠቀሟቸው መሣሪያዎች፣ በአዘፋፈን ስልት (style of vocalization)፣ ከዋኞቹ አባል በኾኑበት ማኅበር (by the association to which the performers belong)፣ ቃል ግጥሞቹ በሚከወኑበት ወቅትና በሌሎች መስፈርቶችም ሊመደቡ እንደሚችሉ ተገልጿል፡፡

በUNESCO (1998) አመዳደብ መሠረት ቃል ግጥሞች በሦስት ሰፋፊ ፈርጆች ተከፋፍለዋል፡፡ ከእነዚህ መካከል የመጀመሪያዎቹ ወቅታዊ ዘፈኖች (occasional songs) የሚባሉት ሲኾኑ፣ እነዚህም በህይወት ዑደት ወቅት የሚቀርቡ ዘፈኖች (በልደት፣ በስም አወጣጥ፣ በጉልምስና ወይም በልጃገረድነት፣ በሰርግና በሞት ወቅት)፤ የሥራ ዘፈኖች (በተወሰኑ ሥራዎች ማለትም በግብርና፣ በአደን፣ በዓሳ ማስገር፣ በሸማ ሥራ ወቅት)፣ በሃይማኖት ሰገዳና በአምልኮ ወቅት የሚቀርቡ ቃል ግጥሞች፣ በቤተ መንግሥት የሚቀርቡ የጦርነትና የስድብ ቃል ግጥሞች ናቸው፡፡

በኹለተኛ ደረጃ የተፈረጁት ደግሞ በመዝናኛ ወቅት የሚቀርቡ ዘፈኖች (Recreational Songs) ሲኾኑ፣ በአብዛኛው በዕረፍት ጊዜና በተለየ ወቅት የሚከወኑ ናቸው፡፡ ለዚህም የልጃገረድ ዘፈኖች ለአብነት ይጠቀሳሉ፡፡ በሦስተኛነት የተቀመጡት የልዩ አጋጣሚ ዘፈኖች (Incidental Songs) የሚባሉት ናቸው፡፡ እነዚህም አብዛኛውን ጊዜ በልዩ ልዩ አጋጣሚዎች የሚቀርቡ ሲኾኑ፣ ልጅን ለማስተኛት ወይም ሲያለቅስ ዝም ለማሰኘትና ለማባበል የሚከወኑ ዘፈኖች በምሳሌነት ይጠቀሳሉ፡፡

Finnegan (2012) ደግሞ የቃል ግጥም ዓይነቶችን የሙገሳ (Panegyric)፣ የሐዘን ወይም የእንጉርጉሮ (Elegiac)፣ ኃይማኖታዊ (religious)፣ የሥራ፣ ወቅታዊና ፖለቲካዊ ዘፈኖች (Topical and Political Songs)፣ ስሜት ነኪ (Lyric-Song)፣ ለሕፃናት የሚዜሙ ዘፈኖች በማለት መድበዋል፡፡ ከFinnegan የቃል ግጥሞች ምደባ መካከል ይህ ጥናት ትኩረቱን ያደረገው የወሎ ቦረና ወረዳ አርሶ አደሮች በግብርና ሥራ ወቅት የማዳበሪያ ኬሚካልና ብስባሽ በማሳዎቻቸው ላይ ሲበትኑ፣ ፀረ ዐረም ኬሚካል ሲረጩና የማሳ ላይ እርከን ሲሠሩ በሚያዜሟቸው ቃል ግጥሞች ላይ ብቻ ነው፡፡

## የሥራ ቃል ግጥሞች ምንነት

የሥራ ቃል ግጥሞች ከተለያዩ የሥራ ዓይነቶች ጋር በጥብቅ የተቆራኙ በመሆናቸው አብዛኛውን ጊዜ የጉልበት ሠራተኞች ከባድ ሥራ በሚሠሩበት ወቅት የሥራ ቃል ግጥሞችን በጋራ ማዜማቸው በሚገባ የታወቀ ነው (Finnegan, 2012)፡፡ የሥራ ቃል ግጥሞች አሰልቺነት ያላቸውን ሁሉንም የሥራ ዐውዶች የሚያካትቱ ሲኾኑ፣ ሰብል በሚኮተኮትበት፣ እርሻ በሚታረስበት፣ እኽል በሚታረምበት፣ በሚታጨድበትና በሚወቃበት፣ ጀልባ በሚቀዘፍበት፣ እንጨት በመጋዝ በሚቆረጥበት፣ ዓሳ በሚጠመድበት፣ በሙቀጫ እኽል በሚወቀጥበት፣ ውሃ ከጥልቅ ጉድጓድ በሚወጣበት፣ የንብ ማስፈሪያ ቀፎ በረጅም ዛፍ ላይ በሚሰቀልበት፣ የእንስሳት ቆዳ በሚለሰልስበትና በመሳሰሉት ተግባራት ወቅት የሚዜሙ ናቸው፡፡ በቤት ውስጥ ሴቶችም ብቻቸውን ኾነው እኽል ሲፈጩ፣ በሙቀጫ ሲወቅጡ፣ ስፌት ሲሰፉ፣ ወዘተ. የሚያቀነቅኗቸው ዘፈኖችም በዚሁ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ በጓድ በጓድ ኾነው የሚሠሩ ሠራተኞችም (ለመንገድ ሥራ መኪና በሚጎትቱበት፣ በፋብሪካ ውስጥ በሚሠሩበት እና ማዕድን በሚያወጡበት ወቅት) የራሳቸው የኾነ ቃል ግጥም ይገጥማሉ፡፡ እነዚህ ቃል ግጥሞች ሥራን ለማቃለል፣ ለማስተባበር፣ ወዘተ. የሚያስችሉ መኾናቸው የታወቀ ነው፡፡ በተለይ በገጠር አካባቢዎች ያሉ የግብርና ሥራዎች ለሥራ ዘፈኖች የመከወኛ አጋጣሚዎችን ይፈጥራሉ (Finnegan, 2012)፡፡

በFinnegan አገላለጽ መሠረት የሥራ ቃል ግጥሞች በዋናነት የሥራውን ፍጥነት የሚያቀላጥፉ፣ በሠራተኞች መካከልም የሥራ ተነሣሽነትን የሚፈጥሩ መሆናቸውን መገንዘብ ይቻላል፡፡ Abrahams (1993) እንዳስረዱት የሥራ ቃል ግጥሞች የሠራተኞችን የድካም ሸክም ለማቃለልና እንቅስቃሴያቸውንም ለማመሳሰል የሚዜሙ ናቸው፡፡ እነዚህ በዜማ የሚቀርቡ የቃል ግጥሞች አብዛኛውን ጊዜ የሠራተኞችን

*ማኅበራዊ እና ባህላዊ ሁኔታ የሚያንፀባርቁ ከመሆናቸው በተጨማሪ ልምዳቸውን፣ ተስፋቸውን እና ምኞታቸውን የሚገልጹ ዓይነተኛ መሣሪያ ሆነው ያገለግላሉ።*

## *የሥራ ቃል ግጥም ባሕርያት*

*የሥራ ቃል ግጥሞች በርካታ ባሕርያት ያሏቸው መሆኑን በመስኩ ምርምር ያካሄዱ ምሁራን ገልጸዋል። ከእነዚህ ምሁራን መካከል* Bohlman (1988) *የሥራ ቃል ግጥሞች ጠንካራ የሆነ የምት መዋቅር* (Rhythmic Structure) *አላቸው በማለት አስረድተዋል። ይህ ሲባል ቃል ግጥሞቹ ብዙውን ጊዜ ከከዋኞቹ አካላዊ እንቅስቃሴ ጋር የሚቆራኝ ጠንካራና ቋሚ የሆነ ምት አላቸው። ዜማውም ቢሆን ከሥራው ፍጥነት ጋር ይዛመዳል ማለት ነው።* Bohlman (1988) *በክዋኔው ወቅት እንደሥራው ዓይነት የተለያዩ ቁሶች በአጃቢነት ሊኖሩ ይችላሉ ብለዋል። ለአብነትም የተለያዩ የግብርና መሣሪያዎች፣ መቅዘፊያ፣ መዶሻ፣ ወዘተ. ተጠቃሾች ናቸው።*

*የሥራ ቃል ግጥሞች ጉልህ ባሕርያቸው ድግግሞሻዊ ቅርጽ* (Repetitive Pattern) *ነው በማለት* Nettl (2005) *ገልጸዋል። በእርግጥ ድግግሞሽ የጽሑፍም ሆነ የቃል ግጥም ባሕርይ በመሆኑ በሐረጋት፣ በስንኞችና በአዝማቾች ላይ ድግግሞሽ ይፈጠራል። በሥራ ቃል ግጥሞች ወቅት የሚፈጠረው ድግግሞሽ ግን ጠቀሜታው ቃል ግጥሞችን ለማስታወስ ይረዳል፤ ዘፈኖችን በቀላሉ በቡድን በቡድን ለመከታተልና ለማዜም ያስችላል። ድግግሞሽ የቃል ግጥሙን ምት ያጠናክራል። ከእነዚህ በተጨማሪ ድግግሞሽ የመርሳትን ወይም የመዘንጋትን ችግር እንደሚከላከል* Vansina (1985) *አስረድተዋል። በአውራጅና በተቀባይ መካከል ባለው ምልልሳዊ ቅርጽ የሚቀርቡ የሥራ ቃል ግጥሞች በድግግሞሽ ቅርጽ ላይ የተመሠረቱ ናቸው።*

*ብዙዎቹ የሥራ ቃል ግጥሞች የአቀንቃኝና የተቀባይ መዋቅር ባሕርይ ያላቸው መሆኑን* Kubik (1999) *አመላክተዋል። ይህ ማለት የጉልበት ሥራው በሚተገበርበት ወቅት የቃል ግጥሙ አቀንቃኝ (መሪ) ያዜማል። በሥራው የሚሳተፉት ሌሎች የቡድኑ አባላት ምላሽ ይሰጣሉ። ይህ ዓይነቱ መስተጋብር ደግሞ በሠራተኞቹ መካከል ያለውን አንድነት ያዳብራል ማለት ነው። የሥራ ቃል ግጥሞች በቀላልና በቀጥተኛ ቋንቋ የመዋቀር ባሕርይም ያላቸው በመሆኑ በአብዛኛው ለመረዳት የማያስቸግሩ ናቸው* (Abrahams, 1993)። *ቃል ግጥሞቹም እየተሠራ ባለው ሥራ ከሠራተኞች ልምድና ከአነቃቂ መልዕክቶች ጋር በተያያዙ ጭብጦች ላይ ያተኩራሉ።*

አብዛኛዎቹ የሥራ ቃል ግጥሞች በተለምዶ በቡድን ስለሚከናወኑ የጋራ ተሳትፎ (Communal Participation) ይስተዋልባቸዋል (Jackson, 2004)፡፡ ይህ ባሕርያቸው በሠራተኞች መካከል የአብሮነት ስሜትን ያጎለብታል፡፡ በጋራ የሚከወነው ዝማሬም መደጋገፍን ለመፍጠር ይረዳል፡፡ የሥራ ቃል ግጥሞች የስሜት መውጫ ወይም የመተንፈሻ (Emotional Outlet) ባሕርይ ያላቸው መሆኑን Levine (1977) ገልጸዋል፡፡ ሠራተኞቹ በቃል ግጥሞቹ አማካይነት ስሜታቸውን፣ ብስጭታቸውን፣ ተስፋቸውን፣ ምኞታቸውን፣ ወዘተ. ይገልጹባቸዋል ማለት ነው፡፡ አብሮ ማዜም ጭንቀትን ለማቃለልና የጋራ ልምድንም ለማዳበር ያስችላል፡፡ የሥራ ቃል ግጥሞች የተለያዩ ጭብጦችን (Diverse Themes) የማንጸባረቅ ባሕርይም አላቸው (Joyner, 1999)፡፡ ልዩ ልዩ ከሆኑት ጭብጦች መካከልም እየተከናወኑ ስላሉት የሥራ ዓይነቶች፣ አስቂኝነት ስላላቸው ጉዳዮች፣ የችግር ወይም የተቃውሞ መግለጫዎች፣ የማበረታቻና ችግርን የመቋቋም አስተያየቶች፣ ወዘተ.ተጠቃሾች ናቸው፡፡

ከጽንሰ ሐሳቡ ቅኝት ቀጥሎ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በሂዩማኒቲስ፣ በቋንቋዎች ጥናት፣ በጆርናሊዝምና በኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ በአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ እንደዚሁም በውጭ ቋንቋዎችና ሥነ ፅሁፍ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ማኅበረሰቦች ላይ ብቻ የጥናቶቻቸውን ወሰን አድርገው የተሠሩ ዐሥር የማስተርስና ሦስት የዶክተሬት ዲግሪ (PhD)፣ በድምሩ ዐሥራ ሦስት የቃል ግጥም ጥናቶች ተቃኝተዋል፡፡ ጥናቶቹ በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ እንጂ በቀጣይ በእኔ ጥናት እንደምናየው በማዳበሪያ፣ በብስባሽ (Compost) ፣ በፀረ ዐረምና በዕርከን ሥራ ላይ የተነገሩ የቃል ግጥሞችን አልተመለከቱም፡፡

## የንድፈ ሐሳብ ማሕቀፎች

በዚህ ጥናት በተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተሰበሰቡትን ጥሬ መረጃዎች ለመተንተን በቅድሚያ አገልግሎት ላይ የዋለው ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ (Functional Theory) ነው፡፡ ለዚህ መነሻም በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ ያለው ማንኛውም የሥነ ቃል ዘርፍ መዋቅራዊ፣ ማኅበራዊና ሥነ ልቦናዊ ተግባር አለው በማለት Green (1997) የገለጹ ሲሆን፣ የዚህ ጥናት መረጃዎች የተተነተኑትም ማኅበራዊና ሥነ ልቦናዊ ተግባራትን ባመላከተ ሁኔታ ነው:: የንድፈ ሐሳቡ አራማጆች የነበሩት Radcliffe-Brown እና Malinowski ሲኾኑ፣ ብዙውን ጊዜ ፎክሎር የሚጠናው በተገኘበት፣ ባለበት ወቅት ወይም በተቀረጸበት ዘመን ነው የሚል አስተሳሰብ ነበራቸው (Oring, 1976; Green, 1997)፡፡ የንድፈ ሐሳቡ

አቀንቃኝ የሆኑት Bascom (1954) በበኩላቸው የአንድን ማኅበረሰብ የባህል ዘለቄታነት የመጠበቂያ ብቸኛው መንገድ የሥነ ቃል ተግባራት ናቸው በማለትም ገልጸዋል፡፡ ስለዚህ ንድፈ ሐሳቡ ለመረጃ መተንተኛነት የተመረጠበት ዋናው ምክንያትም ጥናቱ ባካለለው ወረዳ ከሚገኘው አርሶ አደር ማኅበረሰብ የተሰበሰቡት ቃል ግጥሞች ያላቸውን ተግባር ለመመርመር ነው፡፡ በሁለተኛነት የተመረጠው ንድፈ ሐሳብ ደግሞ ክዋኔያዊ (Performance Theory) የተባለው ነው፡፡ ምክንያቱም ያለ ክዋኔ ማንኛውም የሥነ ቃል ዘርፍ ሊኖር አይችልምና ነው (Dundes, 2005)፡፡ በመሆኑም በክዋኔያዊ ንድፈ ሐሳብ አማካይነት ጥናቱ ባካለለው ማኅበረሰብ የሚቀነቀኑትን የቃል ግጥሞች እንደሚከወኑባቸው አጋጣሚዎች መርምሮ ይዘታቸውን መተንተን እንዲቻል ንድፈ ሐሳቡ ሊመረጥ ችሏል ማለት ነው፡፡

## የጥናቱ ዘዴና የመረጃ ምንጮች

ይህ ጥናት ዓይነታዊ ሲሆን፣ ገላጭ የምርምር ስልትን ተከትሎ ተከናውኗል፡፡ ለጥናቱ የሚሆኑት መረጃዎችም በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅና በሰነድ ፍተሻ ተሰብስበዋል፡፡ በምልከታው አርሶ አደሮቹ የተለያዩ የግብርና ሥራዎችን ሲያከናውኑ የሚያዜሟቸውን ቃል ግጥሞች በተፈጥሮ ዐውድ በአካል በመገኘት ለመሰብሰብ ተችሏል፡፡ በዓላማ ተኮርና በጠቋሚ የንሞና ዘዴዎች የተመረጡ ዐሥራ አምስት ሰዎችም በቃለ መጠይቅ ወቅት በመረጃ ሰጪነት ተሳትፈዋል፡፡ ቃለ መጠይቅ ለጥናቱ በመረጃ ምንጭነት የተመረጠበት ዋናው ምክንያት በተፈጥሯዊ ዐውድ በምልከታ አርሶ አደሮቹ የግብርና ሥራዎቻቸውን በሚያከናውኑበት ወቅት ያዜሟቸው ቃል ግጥሞች ለትንተናው በቂ ሆነው ባለመገኘታቸው የተነሣ ነው፡፡ ምንም እንኳን ቃለ መጠይቁ አቀራረቡ ጥያቄያዊ ቢሆንም፣ ቃል ግጥሞቹን ሲነግሩኝ የነበሩት መረጃ ሰጪዎች ግን የተለያዩ የአካል እንቅስቃሴዎችን እና ፈገግታን ያሳዩ ነበር፡፡ ከላይ ከተገለጸው በተጨማሪ፣ በወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት በባህል እሴቶች ዘርፍ ሙያተኞች ተሰብስበው በሰነድነት ከተቀመጡት ቃል ግጥሞች መካከል በቅርጽም ሆነ በይዘት ለእኔ ጥናት ተገቢ ናቸው ያልኳቸውን መርጬ በማሟያነት ለመጠቀም ችያለሁ፡፡


ቃለ መጠይቆቹ ከጥር 19/2012 ዓ.ም. እስከ መጋቢት 05/2012 ዓ.ም.፣ ከሐምሌ 04 — 06/2012 ዓ.ም እና ከመስከረም 04 እስከ 09/ 2013 ዓ.ም ድረስ ተከናውነዋል፡፡ እነዚህ ጊዜያት የተመረጡት አርሶ አደሮቹ እርሻቸውን በማረስ ለዘር እያዘጋጁና እየዘሩ ባሉበት ወቅት

የኬሚካል ማዳበሪያን እና ብስባሽን ሲጠቀሙ፣ በዐረም ወቅትም ቢሆን ቡቃያውን እየኮተኮቱ የኬሚካል ማዳበሪያን ሲበትኑ ቃል ግጥሞችን ያዜማሉ፡፡ እርከን ሲሠሩም ቢሆን እንደዚሁ፡፡ ሰብላቸውን ሲወቁ ደግሞ ቀደም ሲል በተጠቀሱት ግብዓቶች ምርታቸው መጨመሩን ተመልክተው ቃል ግጥሞችን የሚያዜሙ በመሆናቸው ነው፡፡ ቃለ መጠይቁቆቹ በተካሄዱባቸው ጊዜያት ምልከታም ተደርጓል፤ በወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት በሰነድ የተቀመጡ ሰነዶችንም ለመመርመር ተችሏል፡፡

ከላይ በዝርዝር በተገለጹት የመረጃ ምንጮች የተሰበሰቡት ቃል ግጥሞች 508 ሲሆኑ፣ እነዚህም በማስታወሻ ደብተርና በመቅረጸ ድምፅ ተይዘዋል፡፡ በተፈጥሮ ዐውድ የተገኙት መረጃዎች ደግሞ በፎቶና በቪዲዮ ካሜራዎች ተይዘዋል፡፡ ጥናቱ በገለጻ የሚብራራ እና የተለያዩ እውነታዎችን መርምሮ ማግኘትን የሚያካትት በመሆኑ ከ508ቱ የቃል ግጥሞች ውስጥ በቅርፅም ሆነ በይዘት ለጥናቱ አስፈላጊ ሆነው የተገኙትን 24ቱን በተለያዩ ንኡሳን ርእሶች ከፋፍሎ በገላጭ የምርምር ዓይነት የይዘት ትንተና (Content Analysis) ለማድረግ ተችሏል፡፡

## መረጃ ትንተናና ትርጎማ

በደቡብ ወሎ ቦረና ወረዳ የሚገኙ አርሶ አደሮች ኑሯቸው የተመሠረተው በሰብል ምርት ላይ በመኾኑ ምርታማነታቸውን ለማሳደግ የኬሚካል ማዳበሪያን በዘርና በዐረም ወቅት ሲበትኑ፣ የዕርከን ሥራን በኅብረት ሲያከናውኑ፣ እንደዚሁም በብስባሽ (Compost) እና በፀረ ዐረም ኬሚካል አማካይነት ምርታቸው መጨመሩን ሲመለከቱ የቃል ግጥሞችን እንደሚያዜሙ ከመስክ ከተሰበሰቡት መረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ይህንን ኹኔታ በሚከተለው መልኩ በቅደም ተከተል ለማየት ተችሏል፡፡




**የኬሚካል ማዳበሪያ**

የኬሚካል ማዳበሪያ ከ1960 ዓ.ም. ጀምሮ በኢትዮጵያ ጥቅም ላይ የዋለ ሲኾን፣ በእርሻ ማሳ ላይ እየተጨመረ ለሰብል ዕድገትና ምርታማነት አስፈላጊ የኾነውን ንጥረ ነገር ከፍ በማድረግ ላይ ይገኛል (በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ግብርና ቢሮ የ2012/2013 ምርት ዘመን የሰብል አመራረት ፓኬጅ፣ 2012)፡፡ ይህ የሚኾነው 100 ኪ.ግ. ኤን. ፒ. ኤስ. የተባለውን እና 200 ኪ.ግ. የዩሪያ ማዳበሪያን በአንድ ሄክታር መሬት ላይ በትክክለኛው ወቅትና መጠን መጠቀም ከተቻለ ነው፡፡

ከላይ በተጠቀሰው ምንጭ እንደተገለጸው እነዚህን የኬሚካል ማዳበሪያዎች በአገልግሎት ላይ ማዋል የሚቻለው ለኹለት መደቦች በመክፈል ነው፡፡ ይሄውም፣ ⅓ኛው እርሻ እየታረሰ ዘር በሚዘራበት ወቅት በማሳው ላይ ተበትኖ ከዐፈሩ ጋር እንዲቀላቀል፣ ⅔ኛው ደግሞ ሰብሉ ከበቀለ ከ35 እስከ 40 ባሉት ቀናት ውስጥ እየተረጨ በኹለተኛው ዙር የዐረም ወቅት ዐፈር እንዲለብስ በማድረግ ነው፡፡ በዚህ ዓይነት መንገድ ጥቅም ላይ የሚውለው የኬሚካል ማዳበሪያ በእርሻ ሥራ ላይ ለተሰማሩት አርሶ አደሮች የምርት ደረጃቸውን ከፍ በማድረግ ረገድ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል፡፡ ጥናቱ በተካኼደበት ወረዳ ያሉት አርሶ አደሮችም በተወሰነ የእርሻ መሬት ይዞታቸው ላይ የኬሚካል ማዳበሪያን

ተጠቅመው ብዙ ምርት ማምረት መቻላቸውን የሚከተሉት ቃል ግጥሞች ያመላክታሉ፤

ቃል ግጥም 1፡- እኽል አልኾን ብሎ መሬቱ አቅቶ፣
ሕዝቡን አሻሻለው ማዳበሪያ መጥቶ፡፡
(ቃለ መጠይቅ፣ ገንዘቤ በለጠ፣
20/05/2012)

የቃል ግጥሙ የመጀመሪያው ስንኝ እጅግ ስሜት ነኪ ነው፡፡ ምክንያቱም በተለያዩ ሰው ሠራሽና ተፈጥሯዊ አደጋዎች የአርሶ አደሩ ማሳ የዐፈር ለምነቱ ከሚገባው በላይ ተሟጥጧል፡፡ በዚህ የተነሣ ለቀለብ የሚኾን ወይም ለምግብ አገልግሎት የሚውል የአዝርዕት ውጤትን ለማግኘት አዳጋች መኾኑን ከቃል ግጥሙ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመኾኑም ገጣሚው ከማኅበረሰቡ የሕይወት ገጠመኝ በመነሣት ስሜቱን በእዝነ ኅሊናችን እንዲሰማን አድርጓል፡፡ በኹለተኛው ስንኝ ላይ ግን በግብርና ሥራ ላይ የተሰማሩ የኅብረተሰብ ክፍሎች በማሳቸው ላይ ለሰብላቸው ተስማሚና ጠቀሜታ ያለውን፣ በፋብሪካ ተመርቶ የሚቀርበውን እና የልዩ ልዩ ንጥረ ነገሮች ውሑድ የኾነውን ማዳበሪያ በመጠቀማቸው ምርታማ ለመኾን በቅተዋል፡፡ በዚህም በኑሯቸው ላይ ለውጥን እና መሻሻልን ማምጣት ችለዋል በማለት ገጣሚው ለኬሚካል ማዳበሪያው ውዳሴውን አቅርቧል፡፡

ቃል ግጥም 2፡- ተልባ እየዘራሁኝ መሬቱን ሳመክነው፣

ማዳበሪያ መጣ ስንዴን የሚያዝቀው፡፡
(ከወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት የተገኘ ጽሑፋዊ መረጃ፣ 22/05/2012)

ከላይ ከቀረበው ማብራሪያ ጋር በተገናኘ መልኩ በዚህ ቃል ግጥም የመጀመሪያው ስንኝ ላይ አርሶ አደሩ የእርሻ መሬቱ በጎርፍ፣ በነፋስ፣ በተደጋጋሚ በመታረሱ፣ ወዘተ. የተነሣ የዐፈሩ ለምነት እየቀነሰ ኺዷል፡፡ በዚህ ምክንያት የዘራው እኽል ፍሬ ስላልሰጠ መናውን በመቅረቱ ተቸግሯል፡፡ ያን ያኽልም ለም ዐፈር የማይፈልገውን እና ተልባ የተባለውን የሰብል ዓይነት ይሻላል ብሎ ቢዘራውም የፈለገውን ያኽል ውጤት ሊያገኝ ስላልቻለ መሬቱን ሲያመክነው እንደኖረ በምሬት ብሶቱን በቃል ግጥም ገልጿል፡፡ የኬሚካል ማዳበሪያን ተጠቅሞ የተትረፈረፈ የስንዴ ምርት ማምረት በመቻሉ ደግሞ ሐሴት አድርጓል፡፡ በዚህ የተነሣ "ማዳበሪያ መጣ ስንዴን የሚያዝቀው" በማለት ስንኝ አዋቅሯል፡፡

ቃል ግጥም 3፡- ከማዳበሪያው ጋር ዘርን እየዘራን፣

ከገለባም አልፈን ምርቱንም አገኘን፡፡

(ቃለ መጠይቅ፣ ገንዘቤ በለጠ፣ 20/05/2012)

የኬሚካል ማዳበሪያ ያለውን ጠቀሜታ በአወንታዊ መልኩ የተመለከተው አርሶ አደር ከላይ ያለውን ቃል ግጥም ተናግሯል፡፡ ይሄውም ጥናቱ በተካኼደበት ወረዳ ያሉ አርሶ አደሮች ለሰብላቸው ዕድገትና ምርታማነት አስፈላጊ የኾነውን ንጥረ ነገር በውስጡ የያዘውን የኬሚካል ማዳበሪያ በእርሻ መሬታቸው ላይ በትክክለኛው ወቅትና መጠን መጠቀም ችለዋል፡፡ ታዲያ ገጣሚው ከማኅበረሰቡ አብራክ የተገኘ በመኾኑ የስሑነትን (በኹነቱ የመነካትን) ባሕርይ በመላበሱ በአጥጋቢ ኹኔታ በሕይወት ለመቆየት የሚያስችል የምግብ ፍጆታ እኽል ባለቤት ለመኾን በቅተናል፤ ከዚያም አልፎ ከዕለት ተዕለት ሕይወታችን ጋር የጠበቀ ቁርኝት ላላቸው የቤት እንስሳት ቀለብ የሚኾን ገለባም ለማግኘት ችለናል በማለት ደስታውን በቋጠራቸው ስንኞች ገልጿል፡፡

የኬሚካል ማዳበሪያ ለአዝርዕት ያለውን ጥቅም እያወቀ፣ ነገር ግን ያለ ማዳበሪያ ዘሩን ዘርቶ ዝቅተኛ የኾነ ምርት በማግኘቱ ለከፋ ችግር ስለተዳረገ አርሶ አደር የሚጠቁመውን ቃል ግጥም ደግሞ ቀጥሎ እንመልከት፤

ቃል ግጥም 4፡- ጥቅሙ ከማዳበሪያ መኾኑን እያወቅሁ፣

እንዲሁ ዘርቼ ችግሬን አፈስኩ፡፡

(ቃለ መጠይቅ፣ ሙሕዬ ሁሴን፣ 04/11/2012)

ከቃል ግጥሙ መረዳት እንደሚቻለው ለሰብል ተስማሚና ከፍተኛ የኾነ ርባና ያለው፣ እንደዚሁም ከልዩ ልዩ ንጥረ ነገሮች ጋር በመዋሓድ በፋብሪካ ተዘጋጅቶ የሚቀርበው ሰው ሠራሽ ማዳበሪያ ጠቀሜታው ከፍተኛ መኾኑን አርሶ አደሩ ተገንዝቧል፤ በሚገባም ተረድቷል፡፡ ነገር ግን በተደጋጋሚ እያረሰ ባለሰለሰው ማሳ ላይ ማዳበሪያ ሳይጠቀም እኽሉን ቢዘራውም፣ ዘሩ ሙሉ በሙሉ ዐፈሩን ፈንቅሎ በመውጣት ሊበቅል ካለመቻሉም በላይ በሚገባው መጠን ሳይፋፋና ሳያድግ በመቅረቱ አርሶ አደሩ ጥሩ ምርት ማግኘትና ምርታማ መኾን አልቻለም፡፡ በዚህም የሚልሰውና የሚቀምሰው ዐጥቶ ለከፋ ችግር መዳረጉን የቃል ግጥሙ አቀንቃኝ በቋጠራቸው መንቶ ስንኞች ገልጿል፡፡ ምናልባት ወደፊት ከፈጸመው ስሕተት ተመልሶ ቤቱን በማሸነፍ ቁጭቱን ይወጣ ይኾን? የሚል ጥያቄ ከአድማጮች መቅረቡ አይቀሬ ነው፡፡

ቃል ግጥም 5:- ማዳበሪያው እኮ አይከፋም ነበር፣

ለሁሉም ሳይደርሰው በጅምር ባይቀር፡፡

(ቃለ መጠይቅ፣ ዓይናለም በጸና፣ 22/05/2012)

አርሶ አደሮቹ የኬሚካል ማዳበሪያን ተጠቅመው ባገኙት ከፍተኛ ምርት በኑሯቸው ላይ ለውጥ ማምጣት እንደቻሉ ከላይ ከቀረቡት ቃል ግጥሞች ለመረዳት ችለናል፡፡ ከዚህ አንጻር ማዳበሪያን በአዎንታዊ ጎኑ የተመለከቱት ሰዎች እንዳሉ ሁሉ ከስርጭት አንጻር በሚታዩ እንቅፋቶች የተነሣ በአሉታዊነት የሚያዩት አካላት መኖራቸውን የሚያንጸባርቀው ቃል ግጥም ደግሞ ከላይ መቅረቡን መመልከት እንችላለን፡፡ በመኾኑም ማዳበሪያ በማሳ ላይ ሲጨመር የሰብሉን የምርታማነት ደረጃ ከፍ በማድረግ ረገድ ከፍተኛ የኾነ ሚና ስላለው ኬሚካሉን መጠቀሙ መጥፎ አልነበረም፡፡ ነገር ግን በአቅርቦት ማነስ የተነሣ ሁሉም አርሶ አደሮች ማዳበሪያውን ሳያገኙ ሥርጭቱ በጅምር የቀረ መኾኑን ከቃል ግጥሙ መረዳት ተችሏል፡፡ በሥርጭት ዕጥረቱ የተነሣ በሚከሠተው ኢ-ፍትሐዊነት ኅብረተሰቡ ስለሚቆዝም ውጤታማ የመኾን ዕድሉ ዝቅተኛ ሊኾን እንደሚችል ከቃል ግጥሙ ለመገንዘብ አዳጋች አይኾንም፡፡

ቃል ግጥም 6፡- ወጣቱ[1] ተነሣ ማዳበሪያ ዝራ መሬትህን ደልድል፣

ነጭ ጤፍ አምርተህ እንዲትባል ሞዴል፡፡

(ቃለ መጠይቅ፣ ወንድወሰን ታረቀኝ፣ 22/05/2012)

በዚህ የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ወጣቶች ደግሞ ጠንካራዎችና ብርቱዎች፣ እንደዚሁም ሠርተው ያልጠገቡ ናቸው፡፡ ስለዚህ ወጣቶቹ በኑሯቸው ላይ ለውጥን ማምጣት እንዲችሉ ለሥራ መነሣሣት እንዳለባቸው የቃል ግጥሙ አቀንቃኝ ይገልጻል፡፡ በመኾኑም የእርሻ ማሳችሁን ደግማችሁ ደጋግማችሁ በማረስ ካለሰለሳችሁና ካስተካከላችሁ በኋላ ዐፈሩ ለሰብሉ ጠቃሚታ እንዲኖረው የሚያደርገውን፣ በፋብሪካ የሚዘጋጀውን እና የልዩ ልዩ ንጥረ ነገሮች ውሑድ የኾነውን ማዳበሪያ መጠቀም አለባችሁ በማለት ገጣሚው ይመክራል፡፡

በእነዚህ ጥረቶቻችሁም ነጭ ጤፍ ዘርታችሁ፣ ዐጭዳችሁና ወቅታችሁ ጥሩ ምርት ስለምታገኙ ካሁን በፊት ላሉ ወይም ወደፊት በእርሻ ተግባር ለሚሰማሩ አርሶ አደሮች እንደ ምሳሌ ኾናችሁ

[1] በወጣቶችና የስፖርት ሚኒስቴር በኢትዮጵያ ከ15-29 ዕድሜ ያላቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች ወጣት እንደሚባሉ ተደንግጓል (የወጣቶች ብሔራዊ ፖሊሲ፣ ያልታተመ)፡፡

የምትቀርቡና የምትታዩ ትኾናላችሁ፤ በናሙናነትም ትሰየማላችሁ ወይም ሞዴል የሚባል ስም ተሰጥቷችሁ ትሸለማላችሁ በማለት ገጣሚው አዚሞላቸዋል፡፡

በቃል ግጥሞቹ አማካይነት የሚሰጡ ትችቶች ድክመትን ወይም ስሕተትን ለማረም ሲባል የሚቀርቡና ቂም በቀል የሌለባቸው በመኾናቸው ሚዛናዊነትን የጠበቁ ናቸው ተብሎ ይታሰባል፡፡ በዚህ መሠረት በተፈጥሮ ዐውድ የተገኙትን የትችት ቃል ግጥሞች ቀጥለን እንመልከት፤

ቃል ግጥም 7፡- ማዳበሪያ ታዞ ሰው ሁሉ ሲያወጣ፣
ብር የለኝም ይላል አረቄ እየጠጣ፡፡
(ምልከታ፣ ሙሕዬ ሁሴን፣ 04/11/2012)

መረጃውን የሰጠኝ አርሶ አደር በሬዎቹን ጠምዶና ዘሩን ዘርቶ እርሻውን በማረስ ላይ በነበረበት ወቅት ስለማዳበሪያ የተባለ የቃል ግጥም ካለ እንዲነግረኝ በትሕትና ጠየቅሁት፡፡ እሱም ስሙን ከነገረኝ በኋላ ሣቅ በማለት “ምን የማውቀው አለ ብለህ ነው?” በማለት ከላይ የቀረበውን ቃል ግጥም ድምፁን ዘለግ አድርጎ አቀነቀነልኝ፡፡ ቃል ግጥሙ ዐፈሩ ለሰብል ተስማሚና ጠቃሚ ነገር እንዲኖረው የሚያደርገውን፣ በፋብሪካ ተዘጋጅቶ ለአርሶ አደሮች የሚቀርበውን እና የልዩ ልዩ ንጥረ ነገሮች ውሑድ የኾነውን የኬሚካል ማዳበሪያ በአካባቢው ያለ ሰው ሁሉ በነቂስ ወጥቶ እንዲገዛ በቅርብ ባለ ባለሥልጣን ታዝዞ እንደነበር ያመለክታል፡፡ ነገር ግን ወደመሸታ ቤት በመኼድ አረቄ የተባለውን አልኮልነት ያለውን መጠጥ እየተጎነጨ ለማዳበሪያ መግዣ የሚኾን ገንዘብ የለኝም የሚለውን አርሶ አደር በከፍተኛ ኹኔታ የተነቀፈ እንዲኾን አድርጎታል፡፡ ምክንያቱም ገንዘቡን በመጠጥ ከሚያጠፋ ይልቅ ለአዝርዕቱ የሚኾን ማዳበሪያ ገዝቶ ምርታማ በመኾን በኑሮው ላይ ለውጥን እና መሻሻልን ማምጣት ነበረበት በማለት ገጣሚው ተግሣጹን ሰንዝሯል፡፡ መጠጥን አዘውትሮ እየገዛ ከሚጠጣ ሰው ጋር ተመሳሳይ ባሕርይ ያላቸው ሰዎችም “እጅግ ያስደንቃል የኛማ ነገር፤ ሠርተን ባገኘነው ጠጥቶ መስከር፡፡” እያሉ ራሳቸውን ሲተቹ እንደነበር በሕይወት ተመክሮዬ ሰምቼ እንደነበር በዚህ አጋጣሚ ለመጠቆም ወድጃለሁ፡፡

## ብስባሽ

ብስባሽ ሊበሰብሱ የሚችሉ የዕፅዋት ቅሪትን እና የሣር በል እንስሳትን ፍግ በአንድ ላይ አድርጎ ከውሃ ጋር በማዋሓድ በጉድጓድ ውስጥ ተቀብሮ እንዲብላላ ከተደረገ በኋላ ከዐፈር ጋር የሚጨመር የተፈጥሮ ማዳበሪያ ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ ማዳበሪያ ለሰብሎች አስፈላጊ

የኾኑ ንጥረ ነገሮችን በመስጠት፣ የዐፈር ለምነትን በመጠበቅና ውሃ የመያዝ ችሎታን ከፍ በማድረግ የምግብ እኽልን እና የፍራፍሬ ዓይነቶችን ምርት ለመጨመር የሚያስችል ዓይነተኛ ግብዓት ነው (ኃይሉ አርኣያና ሌሎችም፣ 2009)። የቃለ መጠይቁ ተሣታፊ ከነበሩት መረጃ ሰጪዎቹ ያገኘሁት ጭምቃ ሐሳብም እንዳመለከተው በእያንዳንዱ ጉድጓድ ውስጥ ያለ ብስባሽ ተብላልቶ ለመጠናቀቅ ኹለት ወራትን የሚፈጅ ሲኾን፣ የዘር ሥራ ከመካኼዱ ከአንድ ወር ቀደም ብሎ ማሳ ላይ እየተበተነ በእርሻ አማካይነት ከዐፈሩ ጋር እንዲቀላቀል ይደረጋል። በዚህ የተነሣ ብስባሹ በውስጡ የያዛቸውን ንጥረ ነገሮች በቀላሉ ለሰብሎች እንዲደርሱ በማድረግ ምርትን እና ምርታማነትን ማሳደግ ይችላል። ሀገር በቀል በኾነ ዕውቀት የተዘጋጀው ይህ ዓይነቱ ብስባሽ የአርሶ አደሮችን ምርታማነት በማሳደጉ የተነሣ ለቃል ግጥሙ ይዘት ምንጭ መኾኑን ከተከታዮቹ ስንኞች እንመልከት፤

ቃል ግጥም 8፡- ጥሩ ምርት አግኝቼ ልጆቼ እንዲያድጉልኝ፣

እበቱን በጥብጬ ኮምፖስት አቀረብኩኝ።

(ቃለ መጠይቅ፣ አሰፋ ግዛው፣ 08/01/2013)

ከላይ የቀረበውን ቃል ግጥም የተናገረው ግለሰብ ተስፋን ሠንቋል። ምክንያቱም የቀንድ ከብትን እበት ወይም ፍግ በውሃ በጥብጦ ያዘጋጀውን ብስባሽ በማሳው ላይ ከበተነ በኋላ የተትረፈረፈ ምርት አግኝቶ የምግብ ዋስትናውን በማረጋገጥ ከአብራኩ የወጡት ልጆች አድገው ለቁም ነገር እንዲበቁለት ተመኝቷል። እዚህ ላይ ገጣሚው "ልጆቼ" ይበል እንጂ ግጥሙ ግን የትዳር ጓደኛን እና አጠቃላይ ቤተሰብን ያሳስባል። ያለ ትዳር ጓደኛ ልጆችን ማፍራት አይቻልምና። ልጅ ሲባልም ትንሹም ትልቁም፣ ወንዱም ሴቱም በአጠቃላይ ተወልደው ለዐቅመ አዳምና ለዐቅመ ሔዋን እስከሚደርሱ ድረስ በእሱ ትከሻ ሥር የወደቁትን ሁሉ ያጠቃልላል። እዚህ ላይ ገጣሚው ለትዳር ጓደኛውና ያጥንቱ ፍላጭ፣ የሥጋው ቁራጭ ለኾኑት ወገኖቹ ጽኑ የኾነ ቤተሰባዊ ፍቅርና መተሳሰብ ያለው መኾኑን ከቃል ግጥሙ መገንዘብ እንችላለን። ብስባሽ ለምርት እድገት ካለው አስተዋፅኦ በተጨማሪ በምርት ጣዕምና ጥራት ላይ ትልቅ ጠቀሜታ እንዳለው ኃይሉ አርኣያና ሌሎች (2009) ገልጸዋል፡ ፡ በዚህ መሠረት ገጣሚው "ጥሩ ምርት አግኝቼ ልጆቼ እንዲያድጉልኝ" በማለት ዘለላ ስንኝ ያቀነቀነው፣ የተፈጥሮ ማዳበሪያ በኾነው ብስባሽ አማካይነት ከተመረተው እኽል ለአካል ግንባታና እድገት የሚበጅ ምግብ ልጆቹ ማግኘት እንደሚችሉ ለማመላከት ሲል ነው።

ቃል ግጥም 9፡- ኮምፖስትን አፍስሼ እኽል ብዘራበት፣
ጭነት በጭነት ላይ አደራረብኩበት፡፡
(ቃለ መጠይቅ፣ ማርቆስ መክብብ፣ 22/05/2012)

ብስባሽን አዘጋጅቶ በእርሻ መሬት ላይ መበተን በሰብሎች የእድገት ጊዜያት በሙሉ አስፈላጊ እንደኾነ፣ ምርትን ቀጣይነት ባለው መልኩ ማሳደግ እንደሚቻል፣ ዐረምን፣ ተባይን እና በሽታን ለመቆጣጠር እንደሚረዳ መረጃ ሰጪዎች አስረድተውኛል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ብስባሹ ሲዘጋጅ በመብላላት ኺደት በሚፈጠር ሙቀት ዐረሞቹ ስለሚቀቀሉ የመብቀል ችሎታቸው በእጅጉ እንደሚቀንስ፣ ከኬሚካል ማዳበሪያ በተቃራኒው የዐፈር ለምነትን በዘላቂነት ለማሻሻል እንደሚያግዝ በመስክ ቆይታዬ ወቅት የጤፍ ዐረም ሲያርሙ ያነጋገርኳቸው መረጃ ሰጪዎች በሰፊው አብራርተውልኛል፡፡ ከላይ ያለውን ቃል ግጥም የተናገረው ግለሰብም ቀደም ሲል በዝርዝር የቀረቡትን ቁም ነገሮች ተገንዝቦ ደጋግሞ ባረሰው ማሳ ላይ ያዘጋጀውን ብስባሽ በመጠቀም ለምግብ አገልግሎት የሚውል እኽልን መዝራት እንደቻለ ነግሮኛል፡፡ ይህንን ማድረግ በመቻሉም የተትረፈረፈ ምርት ለማግኘት በቅቷል፡፡ በዚህ የተነሣ ምርቱን በጋማ ከብትም ኾነ በመኪና ሲያጓጉዝ አንዱን በአንዱ ላይ እያነባበረ በመጫኑ የተሰማውን የደስታ ስሜት ገልጿል፡፡

ቃል ግጥም 10፡- ዩሪያ ከመግዛት ገንዘብን አውጥቶ፣

መጠቀም ይሻላል ኮምበስ[2] አዘጋጅቶ፡፡

(ቃለ መጠይቅ፣ አብዱ ሙሐመድ፣ 22/05/2012)

ይህንን ቃል ግጥም ያቀነቀነው ገጣሚ ብስባሽን በማሳ ላይ መጠቀም የተትረፈረፈ ምርት ለማግኘት ከማስቻሉም በተጨማሪ "ዩሪያ" ለተባለው የኬሚካል ማዳበሪያ የሚወጣውን የገንዘብ ወጪ ለመቀነስ እንደሚረዳ ምክሩን ለግሷል፡፡ እዚህ ላይ "ዩሪያ" እና ብስባሽ በንጽጽር የቀረቡ መኾኑን ከግጥሙ መገንዘብ ይገባል፡፡ በመኾኑም ብስባሽ ያለ ምንም የገንዘብ ወጪ በአርሶ አደሩ ጉልበት ብቻ ሊዘጋጅ የሚችል በመኾኑ በገንዘብ ተገዝቶ ከሚቀርብ የኬሚካል ማዳበሪያ የተሻለ እንደኾነ መንቶ ስንኞቹ ያስረዳሉ፡፡ በአጭሩ በገንዘብ መልክ በብድር አማካይነት ከሚመጣ ዕዳ ያድናል ማለት ነው፡፡ እዚህ ላይ ለመጠቆም የምፈልገው የኬሚካል ማዳበሪያና ብስባሽ ያሏቸው ንጥረ ነገሮች እኩል ይሁን አይሁን ማጣራቱ

[2] ዘመናዊ ትምህርትን ያልተማሩ አንዳንድ መረጃ ሰጪዎቼ በንበት ችግር ምክንያት ኮምፖስት የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል በትክክል ስለማይጠሩ ‹‹ኮምበስ›› እያሉ ቃል ግሙጥን የነገሩኝ መሆኑን መጠቆም ወድጃለሁ፡፡

የዚህ ጥናት ዓላማ አለመሆኑን ነው፡፡ ነገር ግን ሁለቱም ግብዓቶች ለሰብል እድገትና ምርታማነት ጠቀሜታ ያላቸው ቢኾንም ብርን ወጪ አድርጎ የኬሚካል ማዳበሪያ ከመግዛት ይልቅ ብስባሽን በቀላሉ አዘጋጅቶ በእርሻ ማሳ ላይ መጠቀሙ ፋይዳው የጎላ እንደኾነ ከቃል ግጥሙ መረዳት ይቻላል፡፡

ቃል ግጥም 11፡- በዋጋ በዛብን ከማምጣት ሮሮ

እናዘጋጃለን ኮምፖስትን ከጓሮ፡፡

(ቃለ መጠይቅ፣ ሙስጠፋ ሙሔ፣ 20/05/2012)

ከላይ የቀረበውን ቃል ግጥም የተናገረው ግለሰብ ቀደም ሲል ከቀረበው ማብራሪያ ጋር በተመሳሰለ መልኩ አርሶ በሌ ለኾነው የኅብረተሰብ ክፍል ምክር አዘል አስተያየቱን ሰንዝሯል፡፡ እንደሚታወቀው አርሶ አደሩ ብስባሽን ለማዘጋጀት የሚጠቀምበትን ቁሳቁስ የሚያገኘው ከአካባቢው ነው፡፡ ይሄውም ሊበሰብሱ የሚችሉ የዕፅዋት ቅሪትን እና የሣር በል እንስሳትን ፍግ ከውሃ ጋር አዋሕዶ በጉድጓድ ውስጥ በማብላላት አገልግሎት ላይ እንዲውል የሚደረግ በመኾኑ ገንዘቡ በየጊዜው እየጨመረ በመንግሥት አማካይነት ከሚቀርበው የማዳበሪያ ዕዳ ከመያዝ ያድናል፡፡ የቃል ግጥሙ ገጣሚም ቢኾን የሚነግረን የኬሚካል ማዳበሪያ መግዣ ዋጋ ከልክ ባለፈ ኹኔታ በመቆለሉ የተነሣ ዋይታና ሐዘን ከማሰማት ይልቅ በመኖሪያ ቤት ዙሪያ ባለ ቦታ ላይ ብስባሽን አዘጋጅቶ መጠቀም እንደሚሻል ነው፡፡ ገጣሚው ከአርሶ አደሩ ሕይወት አንጻር ይህን ይበል እንጂ ከዚህም ባለፈ መንግሥት ለኬሚካል ማዳበሪያ የሚያወጣውን የውጭ ምንዛሬ ችግር ሊያቃልልለት እንደሚችል ልብ ማለት ይገባል፡፡

ቃል ግጥም 12፡- ሰነፉ ገበሬ ኮምፖስት ያልቀበረ፣
ዘሩንም ሳያገኝ መና ኾኖ ቀረ፡፡
(ቃለ መጠይቅ፣ አራጋው ሐሰን፣
05/07/2012)

ቃል ግጥሞች በስንፍና ላይ የመሣለቅ ፋይዳ እንዳላቸው Bascom (1954) ገልጸዋል፡፡ ከላይ ያለውን ቃል ግጥም የተናገረው አርሶ አደርም ሰነፍ በኾነው ገበሬ ላይ ትችቱን ሰንዝሯል፡፡ ይሄውም በእርሻ ተግባር የሚተዳደረው ሥራ ጠል ሰው በሰበብ አስባቡ ተቀምጦ እየዋለ የቀንድ ከብት እበትን ወይም ፍግን እና የዕፅዋት ቅሪትን በውሃ ካዋሐደ በኋላ በጉድጓድ ውስጥ ቀብሮ ብስባሽ በማዘጋጀት በእርሻ መሬቱ ላይ

አለመጠቀሙን በመጀመሪያው ስንኝ ላይ አንጸባርቋል፡፡ ታዲያ እንዲህ ያለው ሰው እንደሌሎቹ አርሶ አደሮች የተትረፈረፈ ምርት ሊያገኝ ቀርቶ በማሳው ላይ በዘርነት የተጠቀመውን እኽል እንኳ መመለስ ወይም መተካት አልቻለም፡፡ በዚህ የተነሣ ምንም ነገር ሳያገኝ ባዶ እጁን መቅረቱን ገጣሚው በዓይነ ኅሊናችን እንድናየው አድርጓል፡፡

ቃል ግጥም 13:- ስንፍና ነው እንጂ የሰው ልጅ ጠላቱ፣
ምርትን ይጨምራል በኮምፖስት መዝራቱ፡፡
(ቃለ መጠይቅ፣ ገንዘቤ በለጠ፣ 07/01/2013)

በቃል ግጥሙ የመጀመሪያው ስንኝ ላይ ሰው ለተባለ ጠቅላላ ፍጡር ሁሉ ባላጋራውና ባላንጣው ስንፍና እንደኾነ በጽኑ ተገልጿል፡፡ ስንፍና ደግሞ ዐቅመ ቢስነትን እና ደካማነትን ብቻ ሳይኾን ለሥራ ያለ ቆራጥነት አናሳ መኾንን፣ ቸልተኛነትን፣ ሥራ አለመውደድን ወይም ሥራ መጥላትን፣ እንደዚሁም መቦዘንን ያመለክታል፡፡ በአጭሩ ሥራን አታሳዩኝ ወይም አታምጡብኝ ማለት እንደኾነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለዚህ በግብርና ሥራ የሚተዳደሩት አርሶ አደሮች በሙሉ ለእድገት ማነቆ የኾነውን ስንፍናን እርግፍ አድርገው በመተው ምርትን መጨመር እንደሚገባቸው ቃል ግጥሙ ያስገነዝባል፡፡ ለዚህ ደግሞ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ሊበሰብሱ የሚችሉ የዕፅዋትን ቅሪትና የሣር በል እንስሳትን ፍግ ከውሃ ጋር አዋሕደው በጉድጓድ ውስጥ እንዲብላላ ካደረጉ በኋላ ከዐፈር ጋር በመጨመር የተለያዩ የእኽል ዓይነቶችን መዝራት ይኖርባቸዋል፡፡ በዚህ የተነሣም አርሶ አደሮቹ በማሳቸው ላይ ከነበረው ሰብል የሚያገኙት ምርት ቀድሞ ከነበረው በላይ ውጤቱ ከፍ ይላል፤ ያድጋል በማለት ገጣሚው አዚሟል፡፡

ቃል ግጥም 14:- ዐፈሩን በውሃ በሙጃ አበስብሼ፣
ያንን ሾከኬ ማሳ እንደ ጨው አልሼ፣
ምርቱን ይዤ ገባሁ እንደ ዐፈር አፍሼ፡፡
(ቃለ መጠይቅ፣ ሐዋ እንድሪስ፣ 04/07/2012)

አርሶ አደሩ ብስባሽን አዘጋጅቶ በማሳው ላይ ካለው ዐፈር ጋር በማደባለቅ ምርቱን ማሳደግ እንደሚችል በሦስቱ ስንኞች የተዋቀረው ቃል ግጥም ይገልጻል፡፡ ይሄውም በግጥሙ ውስጥ የተሳለው ገጸ ሰብ የተትረፈረፈ ምርት ለማግኘት በቅድሚያ በክረምት ወራት በብዛት በቅሎ በቶሎ የሚያድገውን እና መስከረም ሲጠባ በፍጥነት የሚጠወልገውን የሙጃ ሣር በመጠነኛ ውሃ አዋሕዶ ብስባሽ ማዘጋጀት እንዳለበት ገልጿል፡፡ ከዚያም እርጥበቱ ቶሎ ከሚለየው ሾከኬ የማሳ ዐፈር ጋር ማደባለቅ እንደሚገባውም አመላክቷል፡፡ በዚህ ሁሉ ተግባርም ሰው ያልሆኑ ነገሮች በንጽጽር ቀርበዋል፡፡ ተነጻጻሪዎቹም የዐፈር ለምነትን ለማሳደግ የሚያገለግለው ብስባሽና ምግብ ጥሩ ጣዕም እንዲኖረው፣

ሳይበላሽ ለብዙ ጊዜ እንዲቆይ የሚያደርገው፣ እንደዚሁም ከመሬት ወይም ከውሃ የሚገኘው ጨው የተባለው ማእድን ናቸው፡፡ ለዕለት ፍጆታ የሚውለው ምግብ ጥሩ ጣዕም እንዲኖረው ጨው እንደሚጨመርበት ሁሉ ሾከኬው ዐፈር ላይም በከፍተኛ ልፋትና ድካም የተዘጋጀውን ብስባሽ በመበተን ምርትን ማሳደግ እንደሚቻል ገጣሚው ያስረዳል፡፡ በዚህ ዓይነት መልኩ የሚገኘው ምርትም ቢኾን እንደ ልብ ከሚዛቅ ዐፈር ጋር ተነጻጽሮ ቀርቧል፡፡ ንጽጽሩም ከተቆፈረ የመሬት አካል የሚገኘውን ዐፈር በቀላሉ ማፈስ እንደሚቻል ሁሉ በገበሬው ማሳ ላይ ያለው እኽልም ከታጨደ፣ ከተወቃ፣ በመጨረሻ ላይም ከእብቅና ከገለባ ከተለየ በኋላ የተጣራውን ከፍተኛ ምርት በእጁ አስገብቶ ወደቤቱ መጓዙን ገጣሚው ባሰናኛቸው ስንኞች ለመግለጽ ችሏል፡፡

## ፀረ ዐረም

ጥናቱ በተካኼደበት ወረዳ የሚገኙ አርሶ አደሮች ምርታቸውን ለማሳደግ ከሚጠቀሙባቸው ግብዓቶች መካከል አንደኛው የፀረ ዐረም ኬሚካል እንደኾነ ቀደም ሲል ተገልጿል፡፡ በዚህ መሠረት በአሁኑ ወቅት አርሶ አደሮቹ ኬሚካሉን በተገቢው ወቅትና መጠን በመርጨት እየተጠቀሙ እንደኾነ በቃለ መጠይቁ ወቅት የተሳተፉት መረጃ ሰጪዎች አስረድተዋል፡፡ ኬሚካሉ የሚከላከላቸው ቅጠለ ሰፋፊ የኾኑትን እና የሣር ዐረሞችን ነው፡፡ ይህን ዓይነቱን ፀረ ዐረም ኬሚካል አርሶ አደሮቹ "መርጦ ገዳይ" በማለት ይጠሩታል፡፡ ከኹለቱ አንዱን ወገን ብቻ መርጦ ስለሚያጠፋ ማለት ነው፡፡ ኹለቱንም የዐረም ዓይነቶች በአንድ ጊዜ የሚገድል ከኾነ ደግሞ "አይመርጤ" ይሉታል፡፡ ምንም እንኳን ሰብልን በተቻለ መጠን በእጅ ማረም ጥሩ ቢኾንም የጉልበት ዕጥረት በሚያጋጥምበትና የዐረሙ ክሥተት ከፍተኛ በሚኾንበት ወቅት ፀረ ዐረም ኬሚካልን መርጨት ተገቢ መኾኑን የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ግብርና ቢሮ (2012) ገልጿል፡፡ ይህንኑ ኹኔታ በመስከረም 06/ 2013 ዓ.ም በተፈጥሮ ዐውድ ባደረግሁት ምልከታ ከጤፍ ዐራሚዎች መካከል በአንዷ ከተነገሩኝ ቃል ግጥሞች መገንዘብ እንችላለን፤

ቃል ግጥም 15፡- ቅጠላ ቅጠሉ ስንዴዬን ሲወርሰው፣
ፀረ ዐረም መጣልኝ የሚበጣጥሰው፡፡
(ምልከታ፣ ገንዘቤ በለጠ፣ 06/01/2013)



*ፎቶግራፍ አንድ፡- ከቶ በተባለው ቀበሌ ወጣት አርሶ አደሮች በ06/01/2013 ዓ.ም. በኅብረት ዐረም እያረሙ በነበሩበት ወቅት እኔም የሥራው ተሳታፊ ነበርኩ፡፡*

ቃል ግጥሙን ያቀነቀነው ግለሰብ በመጀመሪያው ስንኝ ላይ የስንዴ ቡቃያውን አስፈላጊ ያልኾነ፣ ተነቅሎ የሚጣል፣ ብዙ ዓይነት መልክና ባሕርይ ያለው ቅጠለ ሰፋፊ ዐረም ወርሶት ወይም ውጦት ስለነበር ያዘነና የተከዘ ይመስላል፡፡ ቅጠለ ሰፋፊ የኾነውን የዐረም ዓይነት የሚያጠፋና "መርጦ ገዳይ" እያሉ አርሶ አደሮቹ የሚጠሩት ፀረ ዐረም ኬሚካል ደግሞ በነፍሱ እንደደረሰለት በኹለተኛው ስንኝ ላይ ገልጿል፡፡ በዚህም ዐረሙ ቀስ በቀስ እየቀጨጨና እየኮሰመነ እንደሚኼድ፣ ቀጥሎም ተበጣጥሶና ተቆራርጦ እንደሚወድቅ፣ በመጨረሻም የስንዴ ሰብሉ ዐራሙቻ ተወግዶለት ግለሰቡ ከፍተኛ ምርት ሊያገኝ እንደሚችል ተስፋን ሠንቋል፡፡ ይህ በመኾኑም ባለ ውለታው ለኾነው ፀረ ዐረም ኬሚካል ክብርና ምስጋና እንደሚገባው በማመን ሙገሳ አቅርቦለታል፡፡

ቃል ግጥም 16፡- ጥቅሙ ከፍተኛ ዋጋው አነስተኛ፣

ፀረ ዐረም ኬሚካል መጣ ያረም ዳኛ፡፡

(ቃለ መጠይቅ፣ ገንዘቤ በለጠ፣ 06/01/2013)

የሚፈልገውን ነገር በማግኘቱ እርካታ የተሰማው አርሶ አደር ከላይ በቀረው ቃል ግጥም ውስጥ ያሉትን መንቶ ስንኞች አዚሟል፡፡ ይህ ቃል ግጥም የቀረበው በሰውኛ ዘይቤ የቋንቋ አጠቃቀም ስልት ሰው ያልሆነውን ፀረ ዐረም ኬሚካል ሰብዓዊ ተግባርን እንዲፈጽም በማድረግ ነው፡፡ ይኼውም የፀረ ዐረም ኬሚካሉ አገልግሎት እጅግ በጣም የላቀ መኾኑን

ለማሳየት ግሉዝ የኾነውን ነገር ነፍስ እንዲዘራ በማድረግ የዳኛን ባሕርይ አላብሶ በዓይነ ኅሊናችን እንዲንመለከተው አድርጎናል፡፡ ምክንያቱም ዳኛ አንድን ጉዳይ አስመልክቶ ብያኔ፣ ፍርድ፣ ውሳኔ … ለመስጠት ሥልጣን ያለው አካል በመኾኑ ነው፡፡ አርሶ አደሩ ቃል ግጥሙን እንዲያዋቅር ያስቻለው ደግሞ የጉልበት ዕጥረት ስላጋጠመው ሰብሉን በወቅቱ ማረም ባለመቻሉ ዐረም እንደወረሰበት፣ በዳኛ በተመሰለውና ዋጋው ዝቅተኛ በኾነው የዐረም መከላከያ ኬሚካል አማካይነት የነበረበትን የዐረም ተግባር ችግር መቋቋም እንደቻለ የቋጠራቸው ስንኞች እንዲናገሩለት በማድረግ ነው፡፡

ቃል ግጥም 17፡- አዝመራው ቀጭጮ ከመባል የእገሌ፣

እንዴት ነው ፀረ ዐረም አርሶ አደር ገላግሌ፡፡

(ቃለ መጠይቅ፣ ገንዘቤ በለጠ፣ 06/01/2013)

ቃል ግጥሙ በባሕርይና በችሎታ አማካይነት ግላዊ ማንነት የተንጸባረቀበት ይመስላል፡፡ ምክንያቱም “የእገሌ” የሚል ማጠንጠኛ ቃል በመጀመሪያው ስንኝ ላይ ተጠቅሷል፡፡ በመኾኑም በግጥሙ ውስጥ በምናብ የተሳለው ግለሰብ የሚያደርገው ድርጊት ለራሱ ብቻ እንጂ በሌሎች ሰዎች እንዲታወቅበት ያለ መፈለግ ነገር ይስተዋልበታል፡፡ በዚህ መሠረት ከእኽል ጋር ዐብሮ በሚበቅልና ተፈላጊ ባለመኾኑ የተነሣ ተነቅሎ በሚጣል የዕፅዋት ዓይነት ሰብሉ ተወርሶ እያለ ክብሩን ለመጠበቅ ሲል በማሳው አቅራቢያ ባለው መንገድ ወጪ ወራጅ የኾኑ ሰዎች “የእገሌ አዝመራ ዐረም ውጦት ቀረ” እያሉ እንዳይዘባበቱበት ይፈልጋል፡፡ በዚህ የተነሣ ግለሰቡ በራሱ ስንፍናም ይኹን በሌላ ምክንያት ባጋጠመው የጉልበት ዕጥረት ዐረሙን ሊያስወግድ ባለመቻሉ ሰብሉ በሚገባው መጠን ሳያድግና ሳይፋፋ በመቅረቱ ነውሩ ተገልጦበታል፡፡ በግብርና ሥራ ለሚተዳደርና እንደእሱ ዳተኛ ለኾነ ሰው ገመና ከታች የኾነው ፀረ ዐረም ኬሚካል ደርሶለት ከችግሩ መላቀቁን ቃል ግጥሙን ያቀነቀነው ገጣሚ አመላክቷል፡፡

ቃል ግጥም 18፡- ጤፍና ስንዴዬን እንከባከባለሁ፣

ፀረ ዐረም ስላለ መታከት ትቻለሁ፡፡

(ቃለ መጠይቅ፣ ገንዘቤ በለጠ፣ 06/01/2013)

ምንም እንኳን ሰብልን በተቻለ መጠን በእጅ ማረም ጥሩ እንደኾነ ቀደም ሲል የተገለጸ ቢኾንም፣ ቃል ግጥሙን የተናገረው አርሶ አደር ካለበት

የጊዜና የጉልበት ዕጥረት የተነሣ በአዝርዕቱ ውስጥ የሚታየውን ዐረም በወቅቱ ለማስወገድ ሊያቅተው ይችላል፡፡ በዚህን ጊዜ በማኅበረሰቡ አጠራር “መርጦ ገዳይ“ እና “አይመርጤ” የተባሉትን የፀረ ዐረም ኬሚካሎች መጠቀሙ አይቀሬ ነው፡፡ ለዚህም ነው “ፀረ ዐረም ስላለ መታከት ትቻለሁ” እያለ በመመካት ኹለተኛውን ስንኝ የተናገረው፡፡ ስለኾነም፣ አርሶ አደሩ በዋናነት በዐረም ማረም መውጣትና መውረዱ፣ መልፋት መድከሙ ቀርቶለታል፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ በኬሚካሉ አማካይነት የጤፍና የስንዴ አዝመራውን ከዐረም ተከላክሎ በመያዝ ለተሻለ ውጤት ሊበቃ እንደሚችል ተስፋ በማድረጉ የተነሣ ነው፡፡

## የዕርከን ሥራ

የዕርከን ሥራ የዐፈርን ለምነት ከተለያዩ ተፈጥሯዊና ሰው ሠራሽ አደጋዎች በመከላከል ረገድ ያለው ፋይዳ ከፍተኛ ሲኾን፣ የማሳና የጋራ (የተራራ) ላይ በሚሉ ዐበይት ክፍሎች ይከፈላል፡፡ ይህ ጥናት የዐፈርን ለምነት በመጠበቅ ምርትን ለማሳደግ አስተዋፅኦ ባለው የማሳ ላይ ዕርከን ትኩረቱን አድርጓል፡፡

ጥናቱ በተካኼደበት ወረዳ የሚገኙ አርሶ አደሮችም በእርሻ ማሳቸው ላይ የዐፈር ዕጥበትን በመከላከል ምርታቸውን ለማሳደግ በዓመት ውስጥ ከ40 — 60 ያኽል ቀናት በጋራ በመረባረብ የማሳ ላይ የዕርከን ሥራን እንደሚያከናውኑ በቃለ መጠይቁ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡ ለአብነትም በየካቲት 01/ 2012 ዓ.ም. በመጀመሪያው ዙር በመስክ ቆይታዬ ወቅት በቦረና ወረዳ ቀያፊር ቀበሌ ሲካኼድ በነበረው የማሳ ላይ የዕርከን ሥራን ለመመልከት ችያለሁ፡፡

በዚህ ሥራም ወንዶችና ሴቶች የተሳተፉ ሲኾን፣ ለሥራውም አካፋ፣ እንደዚሁም ዛቢያው ቀጥ ያለና ወፍራም ኾኖ በጫፉ ላይ ማረሻ ወይም መጥረቢያ መሰል ዶማ የተዋደደበት መቆፈሪያ ወይም ደንጎራ ይዘዋል፡፡ የዕርከን ሥራው ከመጀመሩ በፊትም ከወረዳ በመጣ ሙያተኛ አማካይነት በጋራ ምክክር አካኺደዋል፡፡ ምክከሩም ያተኮረው ለዕለቱ ሥራ የተመረጡት ማሳዎች የትኞቹ እንደኾኑ፣ በምን ያኽል ርቀት ዕርከኑ መሠራት እንዳለበትና በማሳዎቹ ላይ ድንጋይ ስለማይገኝ የኅርፍ ውሃን ገድበው ሊይዙ የሚችሉ ጉድጓዶችን በቦይ መልክ መቆፈር በሚሉ ነጥቦች ላይ ነበር፡፡ ከምክክሩም በኋላ አርሶ አደሮቹ ለዕርከን ሥራው ወደተመረጡት ማሳዎች ሲጓዙም ኾነ የአንዱ የማሳ ዕርከን ሥራ አብቅቶ ወደሌላው ሲሸጋገሩ እንደዱላ በማጀቢያነት የተጠቀሟቸውን አካፋና ደንጎራ ወደላይ አድርገው “ሆ” ሲሉ ተመልክቻለሁ፡፡ እርስ በርሳቸውም በመቀላለድ እየተሣሣቁ የዕርከን ሥራውን በቀናነት

ሲያከናውኑ እንደነበር ለማየት ችያለሁ፡፡ ይህ ዓይነቱ የዕርከን ሥራ የቃል ግጥሞችን ለመከወን ምቹ አጋጣሚ በመኾኑ ምክርን የሚለግሱ፣ ትችትን የሚሰነዝሩ፣ ጥገኝነትን የሚነቅፉ፣ ታታሪነትን የሚያበረታቱ ግጥሞችን ከአርሶ አደሮቹ በዐውድም ሆነ በቃለ መጠይቅ ለማግኘት ተችሏል፡፡ በማስረጃነት የቀረቡት የሚከተሉት ቃል ግጥሞችም ከላይ የተጠቀሱትን ሐሳቦች የሚያንጸባርቁ መኾናቸውን ማጤን ይገባል፡፡



*ፎቶግራፍ ሁለት፡- በቦረና ወረዳ፣ ቀያፈር ቀበሌ የሚገኙ አርሶ አደሮች በ01/06/2012 ዓ.ም የአንዱን የማሳ ላይ ዕርከን ሥራ ጨርሰው ወደሌላው ሲሸጋገሩ በነበሩበት ወቅት፡፡*

ቃል ግጥም 19፡- አያችሁለት ወይ የዕርከንን ውለታ፣
እኽሉን ሲያዳብረው ሲመቸው መኻታ፡፡
(ምልከታ፣ ይመር ሐሰን፣ 01/06/2012)

በቃል ግጥሙ የዕርከን ሥራው ያደረገውን በጎ ተግባር፣ ወይም መልካም ሥራ ዓይናችሁን እና ልባችሁን ባንድ ላይ አድርጋችሁ ተመለከታችሁት ወይ? ጥቅሙንስ አስተዋላችሁት ወይ? በማለት አቶ ይመር ሐሰን አብረውት ላሉት ሰዎች ጥያቄ እያቀረበ እርከኑን አወድሶታል፡፡ በወረዳው ለሚበቅለውና ለምግብ አገልግሎት ለሚውለው የአዝርዕት ዓይነት (ስንዴ፣ ዐጃ፣ ገብስ፣ ባቄላ፣ ዐተር፣ ሽንብራ፣ አደንጓሬ፣ ጓያ፣ ምስር፣ ማሽላ፣ ዘንጋዳ፣ በቆሎ፣ ጤፍ፣ ወዘተ.) ዕርከኑ የያዘው ለም ዐፈር ስለተመቸው ሰብሉ ቀደም ሲል ከነበረው መጠን የበለጠ እንዲያድግ፣ እንዲፋፋና ከዚያም በላይ ምርቱ ከፍ እንዲል አድርጎታል ሲልም አመስግኖታል፡፡

ቃል ግጥም 20፡- ዐፈራችን ታጥቦ እንዳይሔድ በውሃ፣
ዛሬ ነገ ሳንል ዕርከንን እንሥራ፡፡
(ቃለ መጠይቅ፣ ሙስጠፋ ሙሔ፣ 22/05/2012)

አርሶ አደሮቹ የዕርከን ሥራውን በጋራ በመረባረብ እንደሚያከናውኑ ቀደም ሲል ተገልጿል፡፡ የዚህ ቃል ግጥም ባለቤት የኾነው አርሶ አደርም ለአንድ ኹለት ሰዎች ብቻ አይደለም ምክር አዘል የኾኑ መንቶ ስንኞቹን ያሰናኘው፡፡ በጋራ፣ በአንድነት፣ በመደጋገፍ፣ ወዘተ. ዕርከንን ለሚሠሩት የኅብረተሰብ ክፍል አባላትም ጭምር ነው፡፡ በመኾኑም ለአዝርዕት እድገትና መዳበር አስፈላጊ የኾነው ለም ዐፈር በዝናብ አማካይነት በሚፈጠር ጎርፍ ተጠራርጎ መወሰድ እንደሌለበት ገጣሚው ምክረ ሐሳቡን ለግሷል፡፡ በመቀጠልም የዕርከን ሥራው ጊዜ የማይሰጥ በመኾኑ ዛሬ ነገ እያልን ሳናመነታና ቀጠሮ ሳንይዝ የእርሻ መሬታችን ለም ዐፈር በጎርፍ እየተሸረሸረና እየተጠረገ እንዳይወሰድ ደግፎ በሚይዝ የድንጋይ ካብ በጋራ ተባብረን መሥራት ይገባናል በማለት ገጣሚው ዐፈር ገፊ ለኾኑት ባልንጀሮቹ ጠቀሜታ ያለው ሐሳብ ችሯቸዋል፡፡

ቃል ግጥም 21፡- ዕርከን እሠራለሁ በጧት በማለዳ፣
ዐፈር ተሸርሽሮ በጎርፍ ሳይነዳ፡፡
(ቃለ መጠይቅ፣ አራጋው ሐሰን፣ 04/07/2012)

ከላይ የቀረበው ቃል ግጥም ደግሞ ታታሪነትን፣ ትጋትን፣ ጥረትን ወዘተ. ያመለክታል፡፡ ምክንያቱም ግጥሙን የተናገረው ግለሰብ የዕርከን ሥራው ያለውን ጠቀሜታ አስቀድሞ የተረዳ በመኾኑ ወኔ በተሞላበት ስሜት በጣም ጧት በኾነ ወቅት ከቤቱ ወጥቶ የዕርከን ሥራውን እንደሚያከናውን በመጀመሪያው ስንኝ ላይ ተናግሯል፡፡ ግለሰቡ ይህንን የሥራ ዕቅድ የወሰነው ደግሞ በዕርከን ሥራው ዋዜማ ምሽት ላይ መኾኑን “በጧት በማለዳ” የሚለው ሐረግ ይጠቁማል፡፡ ይህንን ሠናይ ተግባር ለማከናወን የተነሣሣውም በኃይለኛ ዝናብ አማካይነት በሚከሠት ጎርፍ የእርሻ መሬቱ ለም ዐፈር ተሸርሽሮ እንዳይወሰድበት ለማድረግ እንደኾነ ኹለተኛው ስንኝ ያስረዳል፡፡

ቃል ግጥም 22፡- ዐፈር ታጥቦ እንዳይሔድ በነፋስ በጎርፉ፣
ዕርከንን እንሥራ ሁሉም በየዘርፉ፡፡
(ቃለ መጠይቅ፣ አየሉ ከማል፣ 23/05/2012)

ምክር አዘል ቃል ግጥሙን ያዜመው አርሶ አደር በዕርከን መሥራቱ ተግባር ላይ ተሳታፊም፣ ቆስቋሽም ወይም ገፋፊ ኃይል ኾኖ ነው የቀረበው፡፡ ምክንያቱም በኃይል በሚንቀሳቀሰው ንፋስ፣ እንደዚሁም በብላጊና በክረምት ወቅት በሚጥለው ኃይለኛ ዝናም የተነሣ ዐፈርን፣ ሣርን፣ ቅጠልን፣ ድንጋይን፣… በሚወስደው ጎርፍ በአርሶ አደሮቹ የእርሻ መሬት ላይ ያለው ለም ዐፈር ምንም ሳይቀር ሙጥጥ ተደርጎ መወሰዱ

አሳስቦታል፡፡ ስለዚህ በፍጥነት በሚከንፈው ንፋስ በየማሳው ላይ ያለው ለም ዐፈር እየተጠረገ እንዳይወሰድ፣ በዝናብ ወቅትም ቢኾን በብዛት መሬት ለመሬት በሚፈሰው ጎርፍ አማካይነት እንዳይሸረሸር ደግፎ የሚይዘውን የድንጋይ ካብ ወይም የዕርከን ግንባታ ተግባሩን በትክክል እናከናውን በማለት ለሥራ ያለውን ቁርጠኝነት ባቀነቀናቸው ስንኞች ገልጿል፡፡ ለዚህ ተግባርም አቀንቃኙ እገሌ እገሌ ብሎ ሳይል ጠቅላላው የኅብረተሰብ ክፍል አንድም ሳይቀር ከየአካባቢው በመውጣት የዕርከን ሥራውን ማከናወን እንዳለበት መልእክቱን አስተላልፏል፡፡ ምክንያቱም አርሶ አደሮቹ በእርሻ መሬታቸው ላይ የዐፈር ዕጥበትን በመከላከል ምርታቸውን የሚያሳድጉት ዕርከንን በአግባቡ ሲሠሩ እንደኾነ ግለሰቡ በሚገባ ማወቅ በመቻሉ የተነሣ ነው፡፡

ቃል ግጥም 23፡- አፋፍ ላይ ውጣና ለሁሉም ንገረው፣
ነገ ከዕርከን ሥራው እርዳታ አለ በለው፡፡
(ቃለ መጠይቅ፣ አህመድ ጀማል፣ 02/07/2012)

ጥናቱ ባካለለው ወረዳ ባለው ማኅበረሰብ ውስጥ የዕለት ሞት ሲያጋጥም ለመቅበር፣ መርዶም ካለ ለማላቀስ ሰዎች ተራራ ላይ ወጥተው ጥሪ ያስተላልፋሉ፡፡ ጥሪውም ያለ ማቋረጥ ሰፊ የኾነ መልክኣ ምድርን ሊሸፍን ይችላል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በቀበሌ ስብሰባና የሥራ ዘመቻ ሲኖርም ተራራ ላይ ተወጥቶ ጥሪው ይተላለፋል፡፡ በአሁኑ ጊዜ በቀበሌ የሚካኼደውን ስብሰባ ለመሳተፍም ኾነ የሥራ ዘመቻውን ለማካኼድ ማኅበረሰቡ በጣም ስለሰለቸ ጥቅምን ታላሚ ያደረገ ጥሪ ተራራ ላይ በመውጣት እንደሚተላለፍ ከላይ ካለው ቃል ግጥም መገንዘብ እንችላለን፡፡ ስለኾነም ተራራ ላይ ኾነህ ለጠቅላላው የኅብረተሰብ ክፍል በነገው ዕለት የዕርከን ሥራ ከሚሠራበት ቦታ በበጎ አድራጊ ድርጅት አማካይነት የሚቀርብ እርዳታ ይኖራል ብለህ መልዕክት አስተላልፍ የሚል ሐሳብ ከግጥሙ ማግኘት ይቻላል፡፡ ይህ ደግሞ እርዳታው ኖረም አልኖረም ኅብረተሰቡ ሠርቶ ራሱን እንዳይችል ለጥገኝነት መዳረግ ይመስለኛል፤ ምክንያቱም የዕርከን ሥራው ለራሱ ለኅብረተሰቡ እንደሚጠቅም ማሳመን እንጂ በሌላ አካል ወይም ጥላ ሥር ሕይወቱን እንዲመራ ለማድረግ ማሳበብ አይገባምና ነው፡፡

ቃል ግጥም 24፡- ልማትን እናልማ በጋራ ኾነን፣
እድገት አይገኝም ዕርከንን ካልሠራን፡፡
(ከወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት የተገኘ ጽሑፋዊ መረጃ፣ 22/05/2012)

ምንም እንኳን ልማት የሚለው እሳቤ ሰፊና ውስብስብ ቢኾንም የአንድ ሀገር ኅብረተሰብ ካለበት ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ በኢኮኖሚውም ኾነ በማኅበራዊው፣ እንዲሁም በፖለቲካው ዘርፍ የመሻሻል ኹኔታ ማሳየት ሲችል እንደኾነ ሥዩም ተፈራ (1999) ገልጸዋል፡፡ በቃል ግጥሙ ውስጥ ግን ልማት የሚለው ቃል በአግባቡ ቢታረስ ጥሩ ምርት ሊያስገኝ በሚችለው መሬት ላይ ዕርከንን በመሥራት ለምነቱን መጠበቅ ማለት እንደኾነ ማጤን ይገባል፡፡ ዕድገትን ስንመለከት ደግሞ የለውጥ ውጤት በተለይም የዓይነት ለውጥ፣ ከዝቅተኛው ወደከፍተኛው የሚደረግ ሽግግር እንደኾነ የማርክሲዝም ሌኒኒዝም መዝገበ ቃላት (1978) ያስረዳል፡፡ በዚህ መሠረት ከግለኝነት ይልቅ በዐብሮነት ላይ ትኩረቱን ያደረገው የቃል ግጥሙ አቀንቃኝ የእርሻ መሬታችን ለም ዐፈር በተለያዩ የተፈጥሮ ክሥተቶች ተጠራርጎ እንዳይወሰድ በጋራ ኾነን ዕርከንን በመሥራት ልማትን ማልማት አለብን የሚለውን መልዕክት ለማኅበረሰቡ ማስተላለፍ ችሏል፡፡ ይህ ካልኾነ ግን የተሻለ ምርት ልናመርት አንችልም፤ በሕይወታችን ላይም ለውጥን አናመጣም፤ የሀብት ባለቤት ልንኾንም አንችልም በማለት አስገንዝቧል፡፡

በአጠቃላይ፣ ቃል ግጥሞቹ የተተነተኑባቸውን ንድፈ ሐሳቦች በተመለከተ ከመረጃ ትንተናው መገንዘብ እንደተቻለው Bascom (1954) የሥነ ቃል ተግባራት ብሎ ከዘረዘራቸው መካከል አንደኛው ባህላዊ ዕሳቤዎችን እና ዕውቀትን ለማስተማርና ለማጠናከር እንደሚውል የገለጸው ጉዳይ በዚህ ጥናትም ተረጋግጧል፡፡ ይኼውም በአርሶ አደሮቹ የተነገሩት ቃል ግጥሞች ብስባሽን አዘጋጅቶ በእርሻ መሬት ላይ መበተን ምርትን ቀጣይነት ባለው መልኩ ማሳደግ እንደሚቻል ማስተማራቸውን ለመረዳት ተችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በሥነ ቃል አማካይነት በማኅበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ካላቸው ባህርያት የሚያፈነግጡ ሰዎች እንደሚወገዙ Bascom (1954) ገልጿል፡፡ ይህንኑ ሁኔታም በእርሻ ተግባራት ላይ ተገኝቼ በምልከታ መረጃ በሰበሰብኩበት ወቅት ወደመሸታ ቤት በመሄድ አረቄ የተባለውን አልኮልነት ያለውን መጠጥ እየተጎነጨ ለማዳበሪያ መግዣ የሚሆን ገንዘብ የለኝም የሚለውና በሰበብ አስባቡ ተቀምጦ እየዋለ ብስባሽ ማዘጋጀት ያልቻለው አርሶ አደር በቃል ግጥም መወገዙን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ የቃለ መጠይቅ ተሳታፊ ከነበሩት መካከልም በፋብሪካ የሚዘጋጀውን እና የልዩ ልዩ ንጥረ ነገሮች ውሁድ የሆነውን ማዳበሪያ በመጠቀም ምርታችሁን ማሳደግ አለባችሁ የሚሉ መልዕክቶችን ያዘሉ ቃል ግጥሞችን ፈገግታ በተሞላበት ሁኔታ ነግረውኛል፡፡ ለጥናቱ በተመረጠው ወረዳ ያሉ አርሶ አደሮች የማሳ ላይ ዕርከን እየሠሩ እያሉ የከወኗቸውን ቃል ግጥሞች በአካል ተገኝቼ በተፈጥሮ ዐውድ የሰበሰብኩ ሲሆን፣ ቃል ግጥሞቹም ዕርከንን ጠንክሮ

ሠርቶ የዐፈርን ለምነት በመጠበቅ ምርታማነትን ማሳደግ እንደሚቻል በአጠቃላይ በእርሻ ሥራ ለሚተዳደረው ማኅበረሰብ ማስተማር መቻላቸውን በተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

## ማጠቃለያና የይሁንታ ሐሳቦች

የዚህ ጥናት ዓቢይ ዓላማ ከመስክ በተሰበሰቡት ቃል ግጥሞች ላይ የይዘት ትንተና ማካኼድ ነው፡፡ ጥናቱ ዓይነታዊ የምርምር ዘዴን እና ገላጭ የምርምር ዓይነትን የተከተለ ሲኾን፣ የዓላማ ተኮርን እና የጠቋሚ የንሞና ዘዴዎችን በአገልግሎት ላይ እንዲውሉ አድርጓል፡፡ በእነዚህ የንሞና ዘዴዎች አማካይነት ጥሬ መረጃዎቹ በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅና በሰነድ ፍተሻ ከመስክ ከተሰበሰቡ በኋላ አንድነት ያላቸውን ርእሰ ጉዳዮች በየፈርጃቸው በመመደብ መልዕክታቸው በይዘት የትንተና ስልት ማብራሪያ ተካኺዶባቸዋል፡፡

በዚህ መሠረት ጥናቱ በተካሄደበት ወረዳ ያሉት አርሶ አደሮች የማዳበሪያ ኬሚካልን ተጠቅመው ብዙ ምርት ማምረት መቻላቸውን ከመስክ ከተሰበሰቡት ቃል ግጥሞቸ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አርሶ አደሮቹ ብስባሽ የተባለውን የተፈጥሮ ማዳበሪያ በማሳቸው ላይ ካለው ዐፈር ጋር በመቀላቀል ምርታማነትን ማሳደግ የቻሉ መኾኑን ካዜሟቸው ቃል ግጥሞች ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ምንም እንኳን በሰብል ውስጥ ያለውን ዐረም በተቻለ መጠን በእጅ በማረም ማስወገዱ ጥሩ ተግባር እንደሆነ የጽንሰ ሐሳብ ቅኝቱ ቢያመላክትም ዐረሙ አዳጋች በሚኾንበት ወቅት ግን ፀረ ዐረም ኬሚካልን ተጠቅሞ ዐረምን በማስወገድ ከፍተኛ ምርት መገኘት መቻሉን የተቀነቀኑት ቃል ግጥሞች አመላክተዋል፡፡

ከላይ ከቀረቡት ግኝቶች በተጨማሪ፣ የእርሻ መሬት ለም ዐፈር በጎርፍ አማካይነት እየተሸረሸረና እየተጠረገ እንዳይወሰድ የማሳ ላይ ዕርከንን በመሥራት ምርትን ማሳደግ እንደሚቻልም በአርሶ አደሮቹ ከተዜሙት ቃል ግጥሞች ለመረዳት ተችሏል፡፡ በመጨረሻም፣ ሌሎች የፎክሎር ተመራማሪዎች፣ ጥናቱ በተካሄደበት ወረዳ የሚገኙ አርሶ አደሮች ምርታማነትን ሊያሳድጉ በሚችሉ ግብዓቶች ላይ የተናገሯቸውን ቃል ግጥሞች በስፋት ሰብስበው ትንተና ቢያካሂዱባቸው የሚል የይሁንታ ሐሳብ በአጥኚው ቀርቧል፡፡ ምክንያቱም ቃል ግጥሞቹ ካለፈው ትውልድ አንሥቶ አሁን እስካለንበት ጊዜ ድረስም ኾነ ወደፊት አፋዊ በኾነ መንገድ የሚተላለፉ በመኾናቸው በኅብረተሰቡ ዘንድ የታሪክና የዕውቀት ማቆያ መዘክር ኾነው ሊያገለግሉ ይችላሉ፡፡

## ምስጋና

ይህን ጥናት ሳይታክቱ በተደጋጋሚ በማረምና በማስተካከል ክፍ ያለ ሙያዊ ድጋፍ ላደረጉልኝ መምህሬና አማካሪዬ ለነበሩት ለዘሪሁን አስፋው (ተባባሪ ፕሮፌሰር)፣ እንደዚሁም ለሙሐመድ ዐሊ (ዶ/ር) ላቅ ያለ ምስጋና ይገባቸዋል፡፡ የትምህርት ዕድል የሰጡኝና የገንዘብ ድጋፍ ያደረጉልኝ የአዲስ አበባና የወሎ ዩኒቨርሲቲዎች በያሉበት ምስጋናዬ ይድረሳቸው፡፡ በወሎ ቦረና ወረዳ በተደጋጋሚ በቆየሁባቸው ቀናት አስፈላጊ የኾኑ መረጃዎችን በመስጠት ቀና ትብብር ያደረጋችሁልኝ የወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት ኃላፊና የባህል እሴት ተጠሪ፣ እንደዚሁም የቃለ መጠይቁ ተሣታፊዎች በሙሉ አመሰግናችኋለሁ፡፡

## የጥቅም ግጭት

ይህ ጥናት ከማንኛውም የጥቅም ግጭት ነጻ ነው፡፡

## ማጣቀሻዎች

ማርክሲዝም ሌኒኒዝም መዝገበ ቃላት*፡፡* (1978)፡፡ አዲስ አበባ፣ ኲራዝ አሳታሚ ድርጅት፡፡

ሥዩም ተፈራ፡፡ (1999)፡፡ *ኢትዮጵያ ከአንድ ትውልድ በኋላ፤ትምህርትና ልማት በኢትዮጵያ፡፡* አዲስ አበባ፣ ርህቦት አሳታሚ ድርጅት፡፡

ኃይሉ አርኣያና ሌሎችም፡፡ (2009)፡፡ *የፌዴራል ግብርና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር ለክልልና ወረዳ ባለሙያዎች አዘገጃጀትና አጠቃቀም ላይ ያተኮረ ቴክኒካል ማኑዋል፡፡* አዳማ (ያልታተመ)፡፡

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ግብርና ቢሮ፡፡ (2012)፡፡ *የ2012/2013 ምርት ዘመን የሰብል አመራረት ፓኬጅ፡፡* ባሕርዳር (ያልታተመ)፡፡

ፈቃደ አዘዘ፡፡ (1991)፡፡ *የሥነ ቃል መምሪያ፡* አዲስ አበባ፣ ኢትዮ ጥቁር አባይ አታሚዎች፡፡

Abrahams, Roger, D. (1993). *Singing the Master; the Emergency of African American Culture in the Plantation.* South Pantheon Books, https://scholarworks.ju.edu.

Alembi, E. (2002). *The Construction of the Abanyole perceptions on Death through Oral Funeral Poetry.* Department of Helsinki University, Finland. https://scispace.com

Anthony, O. & Olajide, Y. B. (2012). *Oral Poetry as Channel for Communication*. Cross-Cultural Communication Editorial Office.https://scispace.com

Bascom, W. (1954). Four Functions of Folklore. *The Journal of American Folklore.* American Folklore Society, *67*(266), 333-349. https://www.marist.edu

Bohlman, P. V. (1988). *The Study of Folk Music in the Modern World*. Indiana University Press. https://iupress.org/

Dundes, A. (2005). Folkloristics in the Twenty- First Century. *The Journal of American Folklore*; *118* (407), 384-408.

Finnegan, R. (1970). *Oral Literature in Africa*. Nairobi: Oxford University press.

Finnegan, R. (1974). How Oral is Oral Literature? *Bulletin of the School of Oriental and African Studies*, University of London, *37*(1), 52-64. https://scholarsbaan.

Finnegan, R. (1977). *Oral Poetry: Its Nature, Significance and social Context*. Cambridge University Press. https://dokumen.pub

Finnegan, R. (2012). *Oral Literature in Africa.* Cambridge: Open Book Publishers. https://books.openbookpublishers.com

Green, A. (ed.) (1997). *Folklore: an Encyclopedia of Beliefs, Customs, Tales, Music, and Art.* Santa Barbara, California Denver, Colorado Oxford, England. https://archive.org

Jackson, B. (2004). *Get Your Ass in the Water and Swim Like Me: African American Narrative Poetry from Oral Tradition.* Harvard University Press. https://archive.org

Joyner, C. (1999). *Shared Traditions: Southern History and Folk Culture.* University of Illinois Press. https://archive.org

Kabira, W. & Mutahi, K. (1988). *Gikuyu Oral Literature*, Nairobi. https://erepository.uonbi.ac.ke

Kamla-Raj. (2007). *The Yorùbá Poets and the Nigerian Economy.* Bunmi Olujinmi General Studies Department, The Polytechnic, Ibadan, Nigeria. http://krepublishers.com

Kubik, G. (1999). *Africa and the Blues.* University Press of Mississippi. https://repuplishers.com

Levine, L. W. (1977). *Black Culture and Black Consciousness: Afro-American Folk Thought from Slavery to Freedom.* Oxford: Oxford University Press. https://api.pageplace.de

Nettl, B. (2005). *The Study of Ethnomusicology: Thirty-One Issues and Concepts.* University of Illinois Press. https://www.academia.edu

Okpewho, I. (Ed.). (1985). *The Heritage of African Poetry.* London: Longman. https:www//camprige.org

Okpewho, I. (1992). *African Oral Literature: Background, Character, and Continuity.*Bloomington and Indianapolis; Indiana University Press. https://citeseerx.ist.psu.edu

Oring, E. (1976). Three Functions of Folklore: Traditional Functionalism as Explanation in Folkloristics. *The Journal of American Folklore Society*, 89(351), 67-80. https://egyankoosh.ac.in

Peek, M. & Yankah, K. (Ed). (2004). *African Folklore: And Encyclopedia*. Routledge https://api.pageplace.de

UNESCO. (1998). UNESCO - WIPO World Forum – on the Protection of Folklore – Thailand, Bildangentu, A.g.

Vansina, J. (1985). *Oral Tradition as History.* London: The University of Wisconsin Press. https://archive.org